በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

ቅዱሳን ንዋያት



በአፍሪካ ጤና ኮሌጅ ለገሀር ጊቢ ጉባኤ

በመዝሙርና ኪነ ጥበባት ክፍል የተዘጋጀ

ህዳር 2018ዓ.ም

ምዕራፍ አንድ ፡-መግቢያ

1.1 የቅድስና ትርጉም..... 3

1.2 የቅድስና አከፋፈል 3

1.2.1 የባሕርይ ቅድስና 3

1.2.2 የጸጋ ቅድስና.....3

1.3 የቅዱሳን መለያ ጠባያት.....4

ምዕራፍ ሁለት፡- ቅዱሳን ንዋያት

2.1 ለሥርዓተ ቅዳሴ የሚያገለግሉና ሌሎች ንዋያት.....5

2.2 ለመዝሙር አገልግሎት የሚውሉ ንዋያት.....12

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ

1.1 የቅድስና ትርጉም

ቅድስና የሚለው ቃል «ቅዱስ» ከሚለው ቃል የተገኘ ነው። በዕብራይስጥ ቅዳሺ› በሱርስት ቃዲሽ› እንዲሁም በአረበኛውና በግዕዝ ‹ቅዱስ› ይባላል። ትርጉሙም ንፁህ ፣ ልዩ ፣ ክብር ፣ የተመረጠ ማለት ነው። ስለዚህም ቅድስና መንጻት ፣መለየት ፣መከበር ፣ መመረጥ በአጠቃላይ ቅዱስ መሆን ማለት ነው።

1.2 የቅድስና አከፋፈል

ሁለት አይነት ቅድስና ሲኖሩ የባህርይና የጸጋ ቅድስና ይባላሉ።

1.2.1 የባሕርይ ቅድስና

- ባህርይ በሁኔታዎች ፣ በጊዜያት የማይለወጥ ሲሆን ቅድስና የባሕርይ ገንዘቡ ለእግዚአብሔር ብቻ ነው። የእግዚአብሔር ባህርይ ስንል በሐዋርያት ሃይማኖት እንደተገለጠው ለእግዚአብሔር ባህርይጉንተ ምክንያት የለውም። ግን የማይታወቅ ባህርይ በፍጥረቱ ተገልጧል። ሮሜ 1፥20 ፥፤2ኛጴጥ 1፥4

ልዑል እግዚአብሔር

- ቅዱስ ነው። ኢሳ 6:3
- ቸርና ለጋስ ነው። መዝ 33፤5
- ብርሃን ነው። ፩ዮሐ 1፤5
- በራሱ ንጹህ ነው። ዕንባ 1፤13
- እውነት ነው ፣ ታማኝ ነው። ዮሐ 1416 ፣ ዘጉ 23፥19
- ባለሙሉ ባለሥልጣን ነው። ሮሜ 9፤15
- አልፋና ኦሜጋ ነው። ራዕ 2116
- ኤልሻዳይ ነው። ዘፍ 17፤1

1.2.2 የጸጋ ቅድስና

- ጸጋ በግሪክ ቃል «ካሪስ» ሲሆን ሞገስ ፤ ፍቅር ፣ ምህረትና ቸርነት በሚል ይተረጎማል። አንድም ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ስጦታ ማለት ነው። ይህም በበጎነት ያለብድራትና ያለዋጋ የሚደረግ ስጦታ ማለት ነው። በመሆኑም ማናቸውም ከእግዚአብሔር የሚገኝ ሀብት ሁሉ ጸጋ ይባላል። መጽሐፍ ቅዱስ በጎነት ፤ ቸርነት ፤ ምህረት ፤ ስጦታ እያለ የሚገልጸው ለእግዚአብሔር የባህርይ ገንዘቡ ስለሆነውና ከእግዚአብሔር ለሰው ልጆች ስለሚሰጠው ጸጋ ነው። መዝ 1511 1 መዝ 33፤5። እግዚአብሔር ጻድቅና ቅዱስ እንደሆነ የእርሱ ፈለግ ተከትለው በቅድስና ሕይወት የተጓዙ ቅዱሳን ይባላሉ። ይህም ከባህርይ ቅድስና (ከእግዚአብሔር ዘንድ) ለፍጥረቱ የተሰጠው ሲሆን እርሱ «ቅዱስ» እንደሆነ እነርሱም ‹ቅዱሳን› ይባላሉ። በአጠቃላይ ለእግዚአብሔር የተለዩ ሁሉ «ቅዱሳን» ይባላሉ።

የጸጋ ቅድስና የተሰጣቸው ፍጥረታት

1. ቅዱሳን መላእክት

2. ቅዱሳን እለታት

3. ቅዱሳን ሰዎች

4. ቅዱሳን ንዋያት

5. ቅዱሳን መካናት

1.3 የቅዱሳን መለያ ጠባያት

- እስከ ሞት ድረስ ይታመናሉ። ራዕይ 2፤1
- በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም የተመሰረተችውን የቤተ ክርስቲያንን እምነትና ስርዓት ጠብቀው በማስጠበቅ አገልግሎት የተጉና የተጋደሉ ናቸው።
- የእግዚአብሔርን ቃል ንባብ ትርጓሜና ምስጢር አያፋልሱም ፤ ምዕመናንንም ያበዛሉ።
- ለክርስቶስ ወንጌል እንደሚገባ ይኖራሉ
- ከአለም ፈጽሞ የተለዩ ናቸው። 1ኛ ዮሐ 1፥15 ፣ ፊል 3፥7-10
- ስለ ሃይማኖት ሲሉ ከፈቃደ ስጋቸው ፣ ከአላውያን ነገስታት ፣ ከመናፍቃን ፣ ከጠንቋዮች፣ ከአህዛብ ፣ ከአጋንንት የሚደርስባቸውን ፈተና በትዕግስት ይቀበላሉ። ገላ 5፥16-17፣ ማቴ10፥17-18፣ ሐዋ16፥16-24፣ 2ኛቆሮ11፥26፣ 1ኛጴጥ5፥18
- ከአለም ተለይተው ፤ በበርሃ ወድቀው ፤ ድንጋይ ተንተርሰው ፣ ጤዛ ልሰው ፤ ዋሻ ዘግተው ስለሃይማኖታቸው በመመስከር እስከ ሰማዕትነት ይደርሳሉ።
- ምትህት ያልሆነ ዕውነተኛ ተዓምራት ያደርጋሉ።
- በህይወታቸው ነውርን አያደርጉም እንዲሁም በሀይማኖታቸው ነቀፌታ አይገኝባቸውም።
- በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን ያገኙ የእግዚአብሔር ባለሟሎች ናቸው። በመሆኑም ለእግዚአብሔር ቅርብ የሆኑ አማላጆች ናቸው።
- ቅዱሳን በአጠቃላይ ምግባር መስራታቸው ፣ በጾም በጸሎት በመወሰናቸው አለምን ያሸንፋሉ።1ኛ ዮሐ 2፥13፣ 4፥4፣ ዮሐ13፥13፣ 2ኛ ቆሮ 11፥23-29

ምዕራፍ ሁለት

ቅዱሳን ንዋያት

ንዋይ፦ ማለት ገንዘብ ፣ጥሪት፣ ቅርስ፣ ወርቅ፣ብር፣ክብት ሌላም ንብረት/ ይህም ማለት ከሣር፤ከእንጨት፣ከማዕድን፣ከብ ረት፣ከጭቃ፣ከቁርበት ከሌላም ሁለ መልክና ቅርጽ ጌጥም ኖሮት የሚዘጋጅ ነው። ወይም እንዲሁ በራሱ ጥሬ ዕቃ ከንብረት ይቆጠራልና ይህም ንዋይ ይባላል።

ቅድሳት፦ ማለት ደግሞ ቅድስና ክብር ንጹሕ ጸጋ ያላቸው የእግዚአብሔር የሆኑ ለእግዚአብሔር አገልግሎት የተለዩ ማለት ነው። «እርሱ ግን ከቅድስናው እንድንካፈል ለጥቅማችን ይቀጣናል, ዕብ.12፥10

ንዋየ ቅድሳት፦ ከተመረጡ የተመረጠ ከተለዩ የተለየ ለዘለዓለም ስሙ የሚኖርበት ምርጥ ዕቃ ማለት ነው። ይህም ስለሆነ ነው ዕቃው ወደ ቤተ መቅደስ ሲገባ ተባርኮና ተፀልዮበት የሚገባው፤ ከቡራክ በኋላ ግን ተራ ዕቃ የነበረው ንዋየ ቅድሳት ሆኖ ለቤተመቅደስ የአምልኮ ሥርዓት መፈጸሚያ የክብር ዕቃ በመሆን በማንም የማይነካ ይሆናል።

በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ለመንፈሳዊ አገልግሎት የሚውሉ ንዋያት ሁሉ የተቀደሱ ናቸው። ምክንያቱም አገልግሎቱ የሚፈጸመው ቅድስና የባሕርይ ገንዘቡ ለሆነው ለልዑል እግዚአብሔር ነውና። አገልጋዮቹ ቅዱሳን ቢታውም ቅዱስ እንደሆነ ሁሉ ንዋያቱም ቅዱሳን ናቸው። ይኸውም ይታወቅ ዘንድ እግዚአብሔር ባለሟሉን ሙሴን፡-

«አንተ ክቡሩን ሸቱ ውሰድ ፤ የተመረጠ ከርቤ አምስት መቶ ሰቅል ፣ ግማሽም ጣፋጭ ቀረፋ ፣ ሁለት መቶ አምሳ ሰቅል ፤ ብርጉድም አምስት መቶ ሰቅል እንደ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን ፣ የወይራ ዘይትም አንድ የኢን መስፈሪያ ትወስዳለህ። በቀማሚም ብልሃት እንደተሠራ ቅመም የተቀደሰ የቅባት ዘይት ታደርገዋለህ። ተቀደሰ የቅብዓት ዘይት ይሆናል። የመገናኛውንም ድንኳን ፣ የምስክሩንም ታቦት ፤ ገበታውንም ዕቃውንም ሁሉ ፣ መቅረዙንም ዕቃውንም ፣ የእጣን መሰዊያና ዕቃውን ሁሉ ፣ የመታጠቢያውን ሰንና መቀመጫውንም ትቀባበታለህ። ሁሉንም ትቀድሳቸዋለህ ! ቅድስተ ቅዱሳንም ይሆናሉ ፤ የሚነካቸውም ሁሉ ቅዱስ ይሆናል» ብሎታል። ዘዳ 30፥22-29።

እንግዲህ በብሉይ ኪዳን ቤተ መቅደስ የነበሩ ንዋያት ይህንን ያህል ቅዱስ ከሆኑ በክርስቶስ ደም ላይ የተመሰረተች በአዲስ ኪዳን ቤተመቅደስ የሚገለገልባቸው ንዋያት ይበልጥ የተቀደሱ ፣ በሚገባ የሚገለገልባቸውንም ይበልጥ እንደሚቀድሱ ማስተዋል ይገባል።

የንዋየ ቅድሳት አዘገጃጀት

ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውሉ የመገልገያ ዕቃ ዎችን ለማዘጋጀት በቅድሚያ የሚሠሩበትን ነገር ማወትና መምረጥ ያስፈልጋል። ከንዋየ ቅድሳት ሁሉ የአበረ ታቦት ነው። ታቦት ደግሞ በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ከማይነቅዝ እንጨት እንዲቀረጽ ታዘዘ። ዘጽ25፥1-9 «እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው ስጦታ ያመጡልኝ ዘንድ ለእስራኤል ልጆች ተናገር በገዛ እጁ ሊሰጠኝ በልቡ የሚያምረው ሰው ሁሉ መባ ተቀበለ። ከእነርሱም የምትቀበሉት መባ ይህ ነው። ወርቅ ፣ብር፤ነሐስ ሰማያዊና ሐምራዊ ተይም ግምጃ ፤ጥሩ በፍታም የአቆስጣ ቁርበት የግራርም እንጨት የመብራትም ዘይት ለቅብዓት ዘይትና ለጣፋጭ ዕጣን ትመም መረግድም ለኢፉድና ዕደረት ኪስ የሚደረግ ፈርጥ በመካከላቸውም አድር ዘንድ መቅደስ ይሥሩልኝ እኔ እንደማሳይህ እንደ ማደሪያው ምሳሌ እንዲሁ ሥሩት።"ዘጽ25፥1-29 ካለ በኋላ ዝቅ ብሎ ዘጸ. 25፥ 10 ላይ ከማይነቅዝ እንጨት ታቦት እነዲሰራ ሲያመለክት «ከግራር እንጨት ታቦት ይሥሩ ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተ ኩል ወርዱም አንድ ክንድ ተኩል ተመቱም አንድ ክንድ ተኩል ይሁን።»ዘጸ. 25፥ 10 በማለት አዘዘ። እንግዲህ ንዋየ ቅድሳትን በምናዘጋጅ ጊዜ ከማይነቅዝና ከጠንካራ ነገር መሆን ይኖርበታል። የንዋየ ቅድሳቱን አዘገጃጀት ከምንና በምን እንደሚሠሩ በዝርዝርና በሥዕላዊ መግለጫ በዚህ መጽሐፍ በየምዕራፎቹ ይገኛሉ።

የንዋየ ቅድሳት አጠቃቀም

ንዋየ ቅድሳት ቀደም ሲል እንዳየነውና ብሎም እንደምንረዳው ለአምላካችን ለልዑል እግዚአብሔር የአምልኮት ሥርዓት በምናከናውንበት ጊዜ ሁሉ የምንገለገልባቸው የተቀደሱ ዕቃዎች ናቸው። ስለሆኑም ስንጠቀምባቸው በቤተ መቅደስ እንዲሁም ጥንቃቄ ሊኖረን ይገባል።

የንዋየ ቅድሳት ምሥጢር

ምሥጢር ማለት ሰው ሳያውቀው እግዚአብሔር ብቻ በሚያውቀው መንገድ የሚከናወን ረቂቅ ሥራ ማለት ነው። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ምድር በተመላለሰበት ጊዜ ሲያስተምር በምሳሌ ነበር። ይኸውም ሁሉም እንደሚገባው በማያውቀው ነገር እየመሰለ ያስተምርነበር፤ ልክ እንደዚሁ ሁሉ ንዋየ ቅድሳትም በምሥጢር የከበሩ በምሳሌ የተነገሩ ናቸው።

2.1 ለሥርዓተ ቅዳሴ የሚያገለግሉና ሌሎች ንዋያት

ለሥርዓተ ቅዳሴ አገልግሎት የምንጠቀምባቸው ቅዱሳን ንዋያት ብዙ ናቸው። ከዚህ በመከተል ስለ ቅዱሳን ንዋያቱና ከሥርዓተ ቅዳሴ ጋር ስላለቸው ግንኙነት በአጭሩ እንዳስሳለን።

- ❖ **ታቦት**

ታቦት ማለት ማደሪያ ማለት ነው። ማደሪያነቱም ለልዑል እግዚአብሔር ነው። በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር አምላክ ታቦትን እንዲያዘጋጅ ሊቀ ነብያት ሙሴን አዞት ነበር። ዘጸ 25፤1-22 ፣ ዘጸ 40፤20፤ ዛሬም በቤተ መቅደስ መሥዋእተ ወንጌል የጌታ ሥጋና ደም ይፈተትበታል። ጽላቱ የሚያድርበትና የጽላቱ ማኖሪያ የሆነው ታቦት የእግዚአብሔር የክብሩ መገለጫ የክብሩም ዙፋን ነው።

ምሥጢሩም፦

- ታቦት የእመቤታችን ጽላት የጌታ አንድም ታቦት የእመቤታችን ጽላት የትስብእት ቃሉ የአካላዊ ቃል ምሳሌ ነው።

❖ ጽላት

ጽላት ማለት ሰሌዳ አንድም መጻለያ ማለት ነው። ጽላት እግዚአብሔር አምላካችን ለሙሴ አስቀድሞ አስርቱን ቃላትን ጽፎ የሰጠው ቃሉ ተጽፎ የሚገኝበት ነው። በጽላቱ ላይ አልፋ ወአ ቤጣ» የሚለው የእግዚአብሔር ስም ይቀረጽበታል።

❖ መንበር

ከወርቅ ፣ ክብር ፣ ከብረት ወይም ከእንጨት ይሰራል። አገልግሎቱም በቤተ መቅደስ ታቦት (ጽላት) ይቀመጥበታል ፤ ጸሎት ይጸለይበታል ፣ መስዋዕት ይሰዋበታል። በመንበሩ ላይበመደበኛነት የሚቀመጡት ንዋያተ ቅዱሳት ታቦትና (ጽላት) ሥዕለ ማርያም ምስለ ፍቁር ወልዳ ሲሆነ በቅዳሴ ጊዜ ሥጋውን ደሙን ለመፈተት የምንገለገልባቸው ጻሕል ጽዋዕ ማኅፈድ ፤ ዕርፈ መስቀል ፣ መስቀል ዕጣን ይቀመጡበታል። መንበሩን የሚዳስሱትና የሚያገለግሉበት ቀሳውስት ናቸው ዲያቆናት ግን ከበው ይቆማሉ።

ምሥጢሩም፦

- መንበር የእመቤታችን ታቦት (ጽላት) የጌታ አንድም መንበር የመንበረ ጸባዖት ታቦት (ጽላት) የጌታ ልዑካን የሠራዊተ መላእክት ምሳሌ ናቸው።

❖ አትሮንስ

በመንበሩ አጠገብ ይቆማል ፤ ካህነ የሚቀድስበትን መጽሐፈ ቅዳሴ ያስቀምጥበታል።

ምስጢሩም፦

- መጽሐፉ የጌታ አትሮንሱ የእመቤታችን ምሳሌ ነው።

❖ ጽንሓሕ

የዕጣን ማጠኛ ማሻተቻ ነው። የኦሪት ጽንሓሕ ሸምሸር ሸጢን ከሚባል ከማይነቅዝ እንጨት የተቀረፀና በወርቅ የተለበጠ ነበር። ዘሌ 16፤12። ዛሬ ግን ከንጹህ ወርቅ ማዘጋጀት የሚቻል ባለመሆኑ የሚሰራው ከብረት ወይም ከናስ ወይም የወርቅና የብር መልክ ካላቸው እሳት በቀላሉ ከማይጎዳቸው ማዕድናት ነው።

❖ ዕጣን

ቅዳሴን ጨምሮ በሌሎች መንፈሳዊ አገልግሎቶች ጊዜ የሚቀርብ መባዕ ነው ፤ በመሆኑም ንጹሕና ነውር የሌለበት መዓዛው ያማረ ሊሆን ይገባል። በበረሃ ከሚበቅል እንጨት የሚለቀም ነው። መልኩም ነጭ (ጸዓዳ) የሆነ ሲሆን ይህም ሃያ አራቱ ካሕናተ ሰማይ ዕጣንን የተመላ ሰማያዊ ማዕጠንት በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት እየሰገዱ ለዓለም ደኅንነት የሚለምኑ-በት ነው። ራዕ 8፤3-5 ፣ ራዕ 5i8-9:

❖ መሶበ ወርቅ

ጎብስተ ቁርባን ከቤተልሔም ወደ ቤተ መቅደስ የሚመጣበት ነው። አስንደዶ ፣ አክርማ ፣ ከአለላ ፣ ከወርቅ ፣ ክብርና ከሌሎች ከከበሩ ማዕድናት የሚሰራ ነው።

ምሥጢሩ፦

- የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ነው።

❖ ጻሕል

የከቡር ሥጋው ማስቀመጫና ማክበሪያ ነው። ይኸውም ከሸክላ ፣ ከወርቅና ብር ፣ ከነሐስና ከብረት የሚሰራ ነው። የተለየ ቅርጽ የተለየ ምልክት ያለው ነው።

ምሥጢሩ፦

- የከቡር ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበት በረት ቦታ አንድም የመቃብሩ ቦታ ምሳሌ ነው።

❖ ጽዋዕ

ዲያቆኑ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ደም የሚያቀብልበት ንዋየ ቅዱስ ነው። ከወርቅ ክብር ከመዳብ ከነሐስ ወይም ክብረት ይሰራል።

ምሥጢሩ

- የጌታ መቃብር አንድም መላእክት ከጌታ ጎን የፈሰሰውን ደም ተቀብለው በዓለም ሁሉ የረጨበት የብርሃን ጽዋዕ ምሳሌ ነው።

❖ ማኅፈድ

በቁሙ መጠቅለያ ማለት ነው። ማኅፈድ የሚባሉት ለመጠቅለያነት የሚውሉና አምስት የሚሆኑ መጠቅለያ ልብሶች ናቸው። ብዙውን ጊዜ በጥቁር ጨርቅ የሚሰሩ ናቸው። አንድ ጻህሉ ላይይነጠፋል ፣ ሦስቱ ጎብስተ ቁርባን ይሸፈንባቸዋል የቀረው አንዱ ደግሞ የጽዋ መሸፈኛ ነው።

❖ ተቅዋም - መቅረዝ

የመብራት ዕቃ ፣ የቀንዲል ፣ የሻማ ማኖሪያ ፣ የሚቆም ወይም የሚንጠለጠል ባለ ብዙ አጽቅ ማለት ነው።

ምሥጢሩ፦

- መቅረዝ የእመቤታችን ፣ መብራት (ብርሃን) የጌታ ፣ ዘይት የመንፈስ ቅዱስ ፣ ቅርንጫፎቹ የምዕመናን ምሳሌ ነው።

❖ ዕርፈ መስቀል

ማንኪያ ፣ መቅጃ ፣ መጨለፊያ ማለት ሲሆን ከወደ እጀታው መስቀል ይኖረዋል። የሚዘጋጀውም ከወርቅ ፤ ከብር ፤ ከነሐስ ፣ ከብረት ከእንጨት ነው። ነገር ግን ጽዋው ከተሰራበት ቁስ በተመሳሳይ መዘጋጀት አለበት። እርፈ መስቀል አገልግሎቱ ከቡር ደሙን ለቆራቢያንና ቆራቢያት የሚቀበሉበት ዕቃ ነው።

ምሥጢሩ

- እርፈ መስቀል የሱራፌል ጉጠት ምሳሌ ነው።

❖ ማኅቶት

ሥያሜው በመቅረዝ ላይ የሚበራውንና ዲያቆናቱ የሚይዙትን የጧፍ መብራት ያጠቃልላል። ዲያቆናቱ የሚይዙት በምሴተ ኀሙስ አይሁድ ጌታን ሲይዙ አብርተው የያዙትን ችቦ ያስተውሳል።

ምሥጢሩ፡-

- ብርሃነ የሊቃውንት ምሳሌ ነው ፤ ብርሃን ሁሉን እንዲያሳይ ሊቃውንትም የረቀቀውን ምሥጢርይገልጣሉና።

❖ ኩስኩሰት (ሰንና ብርት)

ከነሐስ ፣ ከመዳብ ፣ ከብረት የሚሰራ እንደ መንቆርቆሪያ ያለ መታጠቢያ ነው። ስን ውሃ መያዣው ሲሆን ብርት ደግሞ ማስታጠቢያው ነው።

ምሥጢሩ፡-

- ሰንና ብርት ጲላጦስ <<ከዚህ ሰው ደም ንጹህ ነኝ› ብሎ የታጠበበት ምሳሌ ነው።

❖ ምፍሐም

ለማዕጠንት የሚሆን እሳት የሚቃጠልበት ነው። ቦታውም ከመቅደስ ውጭ በመዘጋጃ ክፍል ወይም በምሥራቅ ደጃፍ ነው።

❖ ጉጠት

ፍሕም የሚያዝበት ነው።

❖ ፍሕም

ለዕጣን ማጠኛ የሚያገለግል ጭስ ከማይበዛበት ተረፈነድ ተመርጦ ይዘጋጃል።

❖ ቃጭል (ቃለ ዓዋዲ ፣ መረዋ)

በቅዳሴ ጊዜ የሚቃጨልና ድምጽን ሚሰጥ ንዋየ ቅዱስ ነው። የሚቃጨለውም ወይም የሚመታው ወደ ቅዳሴ ሲገባ ፣ «ጸዐዑ ንዑሰ ክርስቲያን» ሲባል ፣ በእግዚኡታ ጊዜ ፣ ድርገት ሲወርድ ! በጸሎትና በምህላ ጊዜ ያቃጭላል። በሰሙነ ህማማት ጊዜ ደውልን ተክቶ ያገለግላል። ቃጭል ከብር፣ ከነሐስና ከብረት ሊዘጋጅ ይችላል።

ምሥጢሩ፡-

- በበረሃ የአዋጅ ነጋሪ ቃልን እየተናገረ መንገዱን የጠረገ የቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ ምሳሌ ነው።

❖ ደወል

ከጠንካራ ብረት ወይም ከብረት መሰል ድንጋይ ይዘጋጃል። አገልገሎቱም ሌሊት ከሰዓታትና ማሕሌት በፊት የተኙትን ለመቀስቀስ 15 ጊዜ ይደወላል ፤ በነግህ በሦስት ሰዓት ለዋዜማ ቁመት 12 ጊዜ ይደወላል። በሰርክ ቅዳሴ መግቢያ 3 ጊዜ ይደወላል ፤ በጻዑ ንዑሳን ክርስቲያን ጊዜ 3 ጊዜ ይደወላል ፤ በእግዚአታ ጊዜ 7 ጊዜ ይደወላል ፤ በድርገት ጊዜ 5 ጊዜ ይደወላል።

ምሥጢሩ

- ደውል የነብያት ምሳሌ ነው።

❖ አልባሳት

አልባሳት ማለት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካሕናት ሊቃውንት የሚለብሱአቸው እንዲሁም ንዋየ ቅዱሳት የሚጎናጸፉባቸው የሚሸፈኑባቸው ናቸው። ቀዳስያን ጳጳሳት ፣ መነኮሳት ፣ ቀሳውስትና ዲያቆናት በቅዳሴ ሰዓት የሚለብሱት አልባሳት የልዑካን ልብስ (ልብሰ ተክህኖ) ይባላል።

የቀሳውስት ልብስ

❖ ቀሚስ

በጥንት ዘመን አብደላ ከኒ ቀሚስ የሚባል ነበር ፤ ይህ ልብስ የሚዘጋጀው ከነጭ ልብስ ሲሆን አሁን ግን ከማንኛውም ጌጥነት ካለው ጨርቅ የሚሰራ ነው።

በመጀመሪያ የሚለበስ ልብስ ነው ፤ በልክ እንዲሆን የታዘዘ ሲሆን ፤ ከረዘመ ማሳጠሪያ ሰውነትን ማጠንከሪያ የሚሆን መታጠቂያ አለው። ይህ ልብስ ወጥ ሆኖ እስከተረከዝ የሚደርስ ሲሆን ከጎንና ጎን የተወሰነ ደረጃ ስንጥቅ (ሓጻ) አለው። ቀዳስያን ከመልበሳቸው በፊት በመጠናቸው እየገመቱ እየገመቱ ይለብሳሉ ፤ ከለበሱ በኋላ ቢረዝማቸው መታጠቂያ ይጠቀማሉ እንጂ ሥርዓተ ቅዳሴው እስኪፈጸም አያወልቁትም። ከዚህም በላይ ካባ ይደርቡበታል።

ካህናት ልብሰ ተክህኖ ከመልበሳቸው በፊት በጳጳሳት እንዲያስባርኩ ጳጳስ ካልኖረ ራሳቸው ባርከው እንዲለብሱ ታዟል።

➢ ካባ ላንቃ

❖ ካባ ላንቃ

ከቀሚሱ በላይ የሚውል መደረቢያ ልብስ ነው። ከካባው ጋር ለምድ አብሮ ተሰፍቶ ስለሚገኝ ነው ካባ ላንቃ» የተባለው። የለምዱ እግር ወይም ዘርፍ በየቦታው እንደ ላንቃ ስለሚወርድ ካባ ላንቃ ተባለ።

ልዩ ልዩ ቀለማት ካላቸው ጨርቆች የሚሰራ ነው። ወርቅና ሐሩ አብሮ ተፈትሎ ከተሰራ ጨርቅ ሊሰራ ይችላል። ካሕናት የሚለብሱት ካባ ላንቃ አምስት መንዲል (መርገፍ) አለው።

ልዩ ልዩ ቀለማት ካላቸው ጨርቆች የሚሰራ ነው። ወርቅና ሐሩ አብሮ ተፈትሎ ከተሰራ ጨርቅ ሊሰራ ይችላል። ካሕናት የሚለብሱት ካባ ላንቃ አምስት መንዲል (መርገፍ) አለው።

➢ ሞጣሕት

❖ ሞጣሕት

በአንገት ተጠልቆ ፊት ለፊት የሚወርድ የደረት ልብስ ነው። ይህም በኦሪቱ ኤፉድ የአሮን ልብስ አምሳል ነው። ካባ ላንቃ በተሰራበት መንገድ የሚሰራ ይሆናል

❖ ቆብ (ቀጸላ ፣ ሕባኔ)

በሥርዓተ ቅዳሴ ጊዜ ካህኑ ወይም ቄሱ በራሱ ላይ ደፍቶ የሚገባው ነው።

ምሥጢሩ፦

- የአክሊለ ሦክ ምሳሌ ነው።

የዲያቆናት ልብስ

❖ ቀሚስ

ጌጥነት ካላቸው ጨርቆች የሚሰራ ነው። በመጀመሪያ የሚለበስ ልብስ ነው ! በልክእንዲሆን የታዘዘ ሲሆን ማሳጠሪያ ፣ ሰውነትን ማጠንከሪያ የሚሆን መታጠቂያ አለው

❖ ለምድ ላንቃ

በቀድሞ ዘመን ቀሚሱ ለብቻ ለምዱ ለብቻ ይዘጋጅ ነበር። አሁን ግን ለምዱ ከቀሚሱ ጋር አብሮ ይሰፋል።

❖ ከፋይ ድግድጋት

ከግብጽ ቤተ ክርስቲያን የተወሰደ ሲሆን ዲያቆናት አንዳንድ ጊዜ ለምድና ቀሚስ በመልበስ ፋንታ ቀሚስ ለብሰው በከፋይ መታጠቂያ በመስቀለኛ ቅርጽ ስለሚታጠቁና ስለሚያደገድጉ ከፋይ ድግድጋት ይባላል። በአሁኑ ጊዜ ዲያቆናቱ እየተዉት ሰንበት ተማሪዎች ሲጠቀሙበት ይታያል።

❖ አክሊል (ቆብ)

የራሱ ልብስ ፣ ቀጸላ ፣ መሸፈኛ ፣ ጌጥነት ያለው አክሊል ይባላል። ከመልካም ጨርቅ የሚሰፋ ክብና መሐሉ ላይ መስቀል ቅርጽ ያለበት ሆኖ ይዘጋጃል።

ልብሰ ታቦት

ከመልከ መልካም ጨርቅ የሚዘጋጅ ጌጥና ዘርፍ የተዘጋጀለት ነው። ታቦት የሚከብርበትና የሚጎናጸፈው ነው።

❖ *መጎናጸፊያ*

ትልቅና እና አራት መዓዘን ያለው ባለ ገበር ክወርቀ ዘቦና ከመሳሰሉት የሚሰራ ታቦተ ህጉ የሚለብሰው ለአከብሮተ ስጋ ወደሙ ቤተ ክርስቲያን የምትጠቀምበት መጎናጸፊያ ይባላል። ታቦት በከብረ በዓል ጊዜ ሲወጣ የሚጎናጸፈው ነው።

❖ ቀጸላ

ታቦቱ መጎናጸፊያውን ከተጎናጸፈ (ከለበሰ) በኋላ ከላይ የሚደረብ ባለጌጥ ዘርፍ ልብስ ነው።

❖ ማከበሪያ

ታቦትን የሚያከብር (የሚይዝ) ካሕን በራሱ ላይ የሚጠመጥመው (የሚያደርገው) ነው።

❖ መጋረጃ (መንጦላዕት)

ግርዶሽ ፣ ጥላ ፣ ከለላ ፣ ልብስ ኪዳን ፣ ልባጥ ፣ ሽፋን ማለት ነው። ከጥሩ ጨርቅ መልከኛ ሆኖ ተዘጋጅቶ በሦስቱም የመቅደስ በር የሚደረጉ ናቸው።

❖ ምንጣፍ

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚነጠፍ ነው። ልብስ ከሚዘጋጅበር የወለል ላይ ልብስ ወይም መረገጫና መረማመጃ ነው።

❖ ድባብና ጥላ (ጸላል)

ዘንጉ ከወርቅ ክብር ከብረት ከእንጨት ሊሰራ ይችላል። ጨርቁ ከከበረ ነገር ሆኖ ወርቃማ ቀለም ሆኖ ወርቃማ ቀለም ያለው መርገፍ የወርቅ ወይም የብር የሚዘረጋ (የሚወጠር) ነው። ታቦት በሚከብርበት ጊዜ ጥላ ይዘረጋል። በቅዳሴ ጊዜ ጥላ አገልግሎት አለው። ይኸውም ወንጌል ሲነበብ ቅዱስ ቁርባን ከቤተልሔም ሲመጣ መስቀሉን ይዘው ለማዕጠንት ሲወጡ በአጠቃላይ ከቡር ነገር የሚጠለልበት ነው።

❖ ግምጃ

ከልዩ ልዩ ሐርና ወርቀ ዘቦ የሚሰራ ወይም የሚቀለም ልብስ (በፍታ) ነው፤ አገልግሎቱ ለቅዱሳት መጻሕፍት መሸፈኛና ለሌሎች ንዋያተ ቅዱሳት ልብስ የሚያገለግል ነው።

❖ ማሕደር

ከቆዳ የሚሰራ የቅዱሳት መጻሕፍት መከተቻ ፣ ማኖሪያ ማሳደሪያ ነው።

መስቀል

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ከመሰቀሉ በፊት መስቀል የወንጀለኞች መቅጫ ነበር። በኦሪት ሥርዓት መስቀል ርጉማን ውጉዛን የሚሰቀሉበት (የሚቀጡበት) ነበር በኋላ ግን እርግማናችንን ሽሮ ጌታችን ስለተሰቀለበት የነጻነታችን አርማ ሆኖ ኃይላችንና መዳኛችን ይሆን ዘንድ ተሰጥቶናል። ለዚሁም ቅዱስ ጳውሎስ “ላላመኑት ሞኝነት ነው ለእኛ ላመንበት ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነው» ሲል አስረድቶናል። ፩ኛ ቆሮ ፩፤18: መስቀል ለእኛ ለክርስቲያኖች የድኅነትና የሕይወት አርማችን ነው ፤ መድኅን አለም ክርስቶስ ለዓለም ቤዛ ይሆን ዘንድ ተሰቅሎበታልና። በቤተ ክርስቲያናችን ብዙ አይነት የመስቀልማዘጋጀ (መስሪያ ቁስ) አለ። እነርሱም እንጨት ፣ ወርቅ ፣ ብር ፣ ነሐስ ፣ መዳብና ብረት ይገኙበታል። መስቀል ከእንጨት መቀረጹ ጌታችን የተሰቀለበት ስለሆነ ነው ፤ ወርቅ መስቀል ደግሞ ወርቅ ንጹህ ነው ጌታችን አምላካችን ንጹህ ባሕርይ አምላክ ስለሆነ ነው ፤ የመዳብ መስቀል የአማናዊ ደሙ ምሳሌ ሲሆን የብረት ደግሞ የተቸነከረበት ጎኑን የተወጋበት ምሳሌ ነው።

‹‹መስቀል ኃይልነ ፣ መስቀል ጽንዕነ ፣ መስቀል ቤዛነ ፣ መስቀል መድኃኒተ ነፍስነ ፣ መስቀል ኃይላችን ነው ፣ መስቀል መመኪያችን ነው ፣ መስቀል ቤዛችን ነው ፣ መስቀል የነፍሳችን መዳኛ ነው›››

ለቅዱስ መስቀል ክብር ይገባል ፤ ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት አስቀድሞ ‹አግሮቹ በሚቆሙበት ሥፍራ እንስግዳለን» መዝ 131፤7 እንዳለ ፤መስቀል በዘባነ ኪሩብ ላይ የቆሙት እግሮቹ የሰውን ልጅ ለማዳን ተቸንክረው የዋሉበት የመድኃኒተ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ዙፋኑ ነውና የአክብሮት ስግደት እንሰግድለታለን ፤ እናከብረዋለን።

ቅዱስ መስቀል፡-

- የእግዚአብሔርን ፍቅር የምናስብበት ነው፤
- ዲያቢሎስ ያፈረበት ፣ ሞተ ነፍስ ድል የተነሳበት ነው፤
- ከቡር ደሙ ቅዱስ ሥጋው የተፈተተበት ነው፤

- የመድኃኒታችንን ውለታ የእመቤታችንን እናትነት የምናስብበት ነው፤
- የተዘጋው የገነት ደጅ የተከፈተበት ነው፤
- መንፈሳዊ ኃይል የምናገኝበት ነው፤
- የሰው ልጅ ከሲኦል ነጻ የወጣበት ነው፤
- ቅዱስ መስቀል መመኪያችን ነው፤
- ሥራችንን ሁሉ የምንባርክበት ነው።

የመስቀል አይነቶች

1. የመጻር መስቀል

የመጻር መስቀል በሥርዓተ ቅዳሴ ጊዜ በዲያቆናት እጅ እንዲሁም በካህናት ለቡራኬ የሚይዙት ሲሆን ፤ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ሰበን (መግነዝ) ለሐዋርያት በእርገቷ ጊዜ የሰጠቻቸው ምሳሌ የሆነ አብሮ የሚንጠለጠልበት መስቀል ነው።

2. የእጅ መስቀል

ይህ በቀሳውስት ፣ ቆሞሳት ፣ ጳጳሳት እጅ ቡራኬ የሚሰጡበት ወይም የሚባርኩበት መስቀል ነው። ያለ መስቀል ሥርዓተ ቅዳሴን መፈጸም አይቻልም።

2.1 ለመዝሙር አገልግሎት የሚውሉ ንዋያት

❖ ከበሮ

ከበሮ የሚለው ቃል አታሞ ፣ ነጋሪት ፣ ለክብረ በአል የሚመታ ፣ ትእምርተ ክብር ፣ ጪሂ ፣ተሰሚ ማለት ነው። ከበሮ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ቦታ ተጠቅሷል። ዘጸ 15፤20 ፤ መዝ 150፥4፣ መዝ 80(81)፣ መዝ 149፥3፣ ዮዲት 16፥2

የከበሮ አሰራር፡-

ከበሮ ከክብት ቆዳ ተጠፍሮ ከእንጨት ወይም ከብር የሚሰራ የዜማ መሳሪያ ነው።

ከበሮ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለያየ ቦታ ላይ ተጠቅሷል።መዝ 149፥3፣ ኢሳ 5፥12፣ ዘፍ31፥27

ምሥጢሩ፡-

ከበሮ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው።

- ሽፋኑ (ግምጃ)፡- ለመዘባበቻ አይሁድ ሸፍነው “መኑ ጸፍዓከ ወመነ ኮርአከ ተነበይ ለነ ክርስቶስ ፡ በጥፊ የመታህ ማን ነው? ትንቢት ተናገር እያሉ ይጠይቁት ነበር” ሉቃ 22164 እያሉ የሸፈነበት ግምጃ ምሳሌ ነው። አንድም ዮሴፍና ኒቆዲሞስ በድርብ በፍታ የገነዙበትን መግነዝ ያስረዳል።
- ጠፍሩ፡- ጌታችን 6,666 ጊዜ መገረፉና በሰውነቱ ላይ የወጣውን ስፍር ቁጥርየሌለውን ሰንበር ምሳሌ ነው። አንድም ሰፊውና ጠባቡ እየተያያዙበት መለኮት በሥጋ ማርያም እንደተዋሐደ ፤ አንድም መለኮታዊ ፍቅሩ ወደ ምድር እንደሳበውና እንደተወለደ ያጠይቃል።
- ማንገቻው፡- የተገረፈበት ጅራፍ ምሳሌ ነው።
- አካሉ፡- (በብር ወይም በእንጨት ነው የሚሰራው) የተቀበረበት መቃብር ምሳሌ ነው።አንዱ ሰፊ ወሆኑ የማይመረመር ረቂቅ ሰፊ ፣ ምሉዕ በኩላሄ ፡ በሁሉ ቦታ ያለ የሆነ መለኮታዊ ባህርይን ሲያጠይቅ አንዱ ጠባብ መሆኑ በጠባብ ደረት ፣ በአጭር ቁመት የማይወሰንነው መወሰኑን ፤ መወለዱን ያጠይቃል።
- በውስጡ ያለው ጠጠር፡- በአዲስ መቃብር ውስጥ 3 መዓልትና 3 ሌሊት ማደሩን ሲያጠይቅ ነው።

- ከበሮ ግራና ቀኝ መመታቱ «ዘበእንሪአሃ ለቤተ ክርስቲያን ተጸፋእከ በውስተ ዓውድ ከመትቀድሳ» ያለውን በማስታወስ የግራና የቀኝ ጉንጩ ምሳሌ ነው።
- ድምጹ የወንጌል ወይም "ኤሎሔ ኤሎሔ ላማ ሰበቅታኒ» ምሳሌ ነው። ማቴ 27፥46፣ ማር 15፥34

❖ ጸናጽል

ጸነጸለ ፣ መታ ካለው ግስ የተገኘ ነው። ጸናጽላት በሚባል ጊዜ ብዛትን ጸናጽል በሚልበት ጊዜ ነጠላን የሚያመለክት ሲሆን ትርጉሙም ሻኩራ ፣ ቃጭል እንደማለት ነው።

የጸናጽል አሰራር፡-

ጸናጽል ከነሃስ ፣ ከብርና ከሌላም ማዕድን ሊሰራ የሚችል የዜማ መሳሪያ ነው። ጸናጽል ያማረ ድምጽ ያለው ሆኖ መልክና ልዩ ጌጥ አለው። መዝ 150፥5።

ጸናጽል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለያየ ቦታ ላይ ተጠቅሷል።2ኛ ዜና29፥25፣ ዜና 15፥16፣ 2ኛ ሳሙ6፥5፣ 2ኛ ዜና5፥13፣ ዕዝ3፥10

ምሥጢሩ፡-

ጸናጽል አባታችን ያዕቆብ በፍኖተ ሎዛ ያያት የወርቅ መሰላል ምሳሌ ነው።

- በግራና ቀኝ ያለው ዓምድ፡- የብሉይና የሐዲስ ምሳሌ በሁለቱ ዓምዶች መሐል ያሉት ሁለቱ ቀጫጭን ዘንጎች ያዕቆብ በፍኖተ ሎዛ መላእክት ሲወጡባት ሲወርዱባት ያያት መሠላል ምሳሌ ሆኖ።
- በዘንጎቹ ላይ ያሉት የብረት ቅጠሎች፡- ያዕቆብ በፍኖተ ሎዛ በመሠላል ላይ ሲወጡ ሲወርዱ ያያቸው መላእክት ምሳሌ ነው።በሌላም በኩል የብረት ቅጠሎቹ ብዛት ቢያንስ አምስት ቢበዛ ሰባት ይሆናል። አምስት ሲሆን የአምስቱ አዕማደ ምሥጢር ሰባት ቢሆን ደግሞ በሰባቱ ሰማያት። የብረት ቅጠሎቹ በመጀመሪያ ዘንግ ላይ ሁለት ይሆናሉ፤ ይህም ወልድ ሁለት ልደት ቅድመዓለም ያለ እናት ከአብና ኋላም አዳምን ለማዳን ያለ አባት ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለዱን ። በሁለተኛ ዘንግ ላይ ሦስት ሲሆኑ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ይመሰላል።
- የጸናጽል ድምጹ፡- ያማረና መልካም መሆኑ በመላዕክት ዜማ ይመሰላል። ወዲያና ወዲህ መባሉ የጌታችን በአይሁድ መንገላታት ምሳሌ ነው።
- ጸናጽል የኪዳነ ኖኅ ምሳሌ ነው።

❖ *መቋሚያ*

መቋሚያ ማለት መደገፊያ ፣ መመርኮዣ ማለት ነው።

አሰራሩ፡-

ብዙውን ጊዜ ከእንጨት የሚዘጋጅ እንደ በትር ዘለግ ያለ ከወደ ጫፉ መስቀል ቅርጽ ያለው ነው። በአሁኑ ጊዜ በአብዛኛው የፐ ፊደል ቅርጽ ያለው አሊያም ድቡልቡል የሆነ ነው፤ ከወደ ጫፉ የሚደረገው ነገር የወርቅ፣ የብር፣የነሐስ፤የብረት፣የቀንድና የእንጨት ሊሆን ይችላል።

አገልግሎቱም መደገፊያ፤ መሞርኮዣና መዘመሚያ ነው። ይሽውም ከከበሮና ከፀናጽል ጋር እንዲሁም ብቻውን ማህሌት ላይ በዝማማ.ና በሽብሸባ ያገለግላል።

ምሥጢሩ፡-

- መቋሚያ የአዳም ተስፋ እና ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ በእፀመስቀል ላይ የተሰቀለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው።
- መቋሚያ ያዕቆብ ትእምርተ መስቀል ያለበት በትር በፊቱ እያተመ ይሰግድና ይጸልይ የነበረበት ምሳሌ ነው።
- ካህናት መቋሚያ በትከሻቸው አድርገው ወዲያና ወዲህ ማለታቸው አይሁድ ጌታን በዕለተ ዓርብ መስቀል አሸክመው ወደ ቀራንዮ መውሰዳቸውና ካህናቱ መቋሚያውን ከዜማ ጋርአስማምተው ከመሬት ላይ መጣልና መደሰቃቸው አይሁድ ጌታን «ማነው የመታህ?» እያሉ ተራ በተራ በዘንግ መምታታቸውን ለማስታወስ ነው።
- ሌላው ደግሞ መቋሚውን እንደ ማማተብ አድርገው ከትከሻቸው አንሥተው እንደ ማማተብ አድርገው ከትክሻቸው አንሥተው ወደ መሬት ማሳረፋቸው ሌላም ሰው መቀበሉ /መሰብሰቡ/ እናም ማስቀመጡ ጌታችን መስቀል ተሸክሞ ወደ ቀራንዮ ሲጓዝ ደክሞት ስለነበር ሳንሰቅለውና የልባችን ሳይደርስ ሕይወቱ ያልፍብናል በማለት መስቀሉን ለሌላ ሰው ማሸከማቸውን ለማስታወስ ነው።

❖ መስንቆ

አሰራሩ

መስንቆ አንድ ምስሶና አንድ ክር ያለው የዜማ ዕቃ ነው፡ ክሩ ከፈረስ ጭራ ይዘጋጃል በአንድነት የሚወጠረው ክር ቢበዛ ሰማንያ ቢያንስ አርባ ይሆናል። ለእግዚአብሔር ክብር ይዘመርበታል።

ምሥጢሩ፡-

- መስንቆ የእመቤታችን ምላሌ ነው።
- አንድ ምስሶ መኖሩ ሃይማኖት አንድ መሆኗን
- ክሩ አንድ ወራጅ መሆኑ አንዲት ጥምቀት ፣ የክሩ ጥቅል ብዛት ቢያንስ አርባ መሆኑ ወንዶች በተወለዱ በአርባ ቀናቸው ጥምቀት ማግኘታቸው፣ ቢበዛ ሰማንያ መሆኑ ሴቶች በተወለዱ በሰማንያ ቀናቸው ጥምቀት ማግኘ ታቸውን ነው።
- ክሩ ዕጣን እየተቀባ ይዘመርበታል፤ ይህም ዕጣን የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ሲሆን ክሩ የጥምቀት ሆኖ በመጠመቅ መንፈስ ቅዱስ እንደሚገኝ ያመለክታል።

መስንቆ አምስት ያህል መሰቀል ይታይበታል

ሀ. የምሰሶ አናት ላይ

ለ. መቃኛው ከምሰሶ ጋር ሲተያይ

ሐ. የመስንቆ ሳጥን ቅርጽ

መ. የክር መወጠሪያ በርኩማ አክር ጋር ተመሳት ሲታይ

ሠ. መከርከሪያው በመስንቆ ክር ጋር እልፎ ሲከረክር አምስት መስቀል መታየቱ አምስቱ ቅንዋተ መስቀል ያስታውሰናል።

❖ እምቢልታ

ከቀርከሀና ከቱቦ መሰል ነገር የሚዘጋጅ የዜማ እቃ ነው። እንደ ዋሽንት የመሰለ ሆኖ በመጠን ትልቅ የሆነ ሲሆን ታቦት ሲወጣ (ሰ.ከበር) ይዘመርበታል ፤ እንዲሁም ነገስታት ግብር ሲያገቡ የሚያስነፉት ፣ ዳዊትም መዝሙር በእምቢልታ ይዘምር ነበር።መዝ 150፥4፣ ዳን3፥10

❖ መለከት

ከኩበት ቀንድ ክብረትና ከሌላም ብረት ነክ ነገር ሊሰራ ይችላል። ለአዋጅ መንገሪያና ለመዝሙር ያገለግላል። መለከት በትንሳኤ ዘጉባኤ የጌታን መምጣት ያበስራል። ማቴ 24፤31 የደስታና የኀዘን መግለጫ ነው። በደስታ ጊዜ ደስታውን ለማብሰር መለከት ይነፋል። በኀዘን ጊዜ ደግሞ ኀዘንን ለመግለጽ መለከት ይነፋል። ሰዎችን ለግዳጅ ያዘጋጃል። በጥንት ጊዜ ሰዎች ለጦርነት ሲጠሩ ነጋሪት ይነሰማል ፤ መለከት ይነፋል። መለኮት ሰዎች ለግዳጅ ዝግጁ እንዲሆኑ ያስጠነቅቃል። ሕዝ 33፤1-6፡

ምስጢሩ፡-

- መለከት የጌታ ዳግም መምጣት ምሳሌ ነው።

❖ ዋሽንት

ከሸንበቆ ወይም ከቀጭን ቀርከሃ ክብረትም ሊሰራ የሚችል የዜማ ዕቃ ነው። ዋሽንት አራት ቀዳዳዎች አሉት።

ምሥጢሩ ፡-

- አራት ቀዳዳዎች በአራቱ ወንገላዊያን ማቴዎስ፤ ማርቆስ፤ሉቃስ፣ዮሐንስ ይመሰላሉ ዳን3፥5፣ ዳን3+10፣ ዳን 3+15

❖ አታሞ

ከእንጨትና ከቆዳ የሚዘጋጅ እንደ ከበሮና ነጋሪት በእጅ የሚመታ ባለ አንድ አፍ ዜማ ዕቃ ነው። ይህ የዜማ ዕቃ በዚህ ዘመን ተጠቃሚ የለውም። «እንዲህም ሆነ ዳዊት ፍልስጥኤማዊውን ገድሎ በተመለሰ ጊዜ እየዘመሩና እየዘፈኑ እልልም እያሉ ከበሮና አታሞ ይዘው ንጉሡን ሳኦልን ሲቀበሉ ሴቶች ከእሥራኤል ከተሞች ሁሉ ወጡ»1ኛ ሳሙ 18፥6 «እነሆም የሰሎ ሴቶች ልጆች አታሞ ይዘው ለዘፈን ሲወጡ ከወይኑ ስፍራ ወጡ» ሳሙ 21፥21

❖ ነጋሪት

ከእንጨትና ከቆዳ የሚሰራ ባለ አንድ አፍ የዜማ ዕቃ ነው። ይህ የዜማ ዕቃ ከአታሞ ጋር ይመሳሰላል ፤ መልእክት ለማስተላለፍና ለክብረ በዓል ማድመቂያ ነው።«ዳዊትና የእስራኤልም ቤት ሁሉ በቅኔና በበገና በመሰንቆም በከበሮም በነጋሪትና በጸናጽል በእግዚአብሔር ፊት በሙሉ ኃይላቸው ይጫወቱ ነበር» 2ሳሙ:6፥5

«በዳግም ምጽአት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለፍርድ ሲመጣ ሚመታ» ዮሐንስ ራእይ

ምሥጢሩ፡-

- የነጋሪት ድምጽ የክርስቶስን ዳግም ምጽአት ያሳስባል።

❖ በገና

በገና ትውፊታዊ፣ ሃይማኖታዊ እና ሰማያዊ የሆነ የዜማ መሳሪያ ነው። በቀደምት ዕብራውያንና በኢትዮጵያውያን ዘንድ እግዚአብሔር በዜማ የሚመሰገንበት እና በርካታ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚቀርብበት በቤተክርስቲያናችን የባለ አውታር(የክር) የዜማ መሣሪያ ከሆኑት መካከል አንዱ ሲሆን በብዙ መልኩም በጣም ጥንታዊ እና ታሪካዊ የሆነ በእድሜው ትልቅነትም ከ አምስት ሺህ ስምንት መቶ ዓመት በላይ እድሜ ያለው፤ ለአውታር መሳሪያዎች አባት ሊባል የሚችል ነው። በተጨማሪም በሰማይም በምድርም አገልግሎት ያለው ለመንፈሳዊ መዝሙር ብቻ የምንጠቀምበት እያንዳንዱን የአካል ክፍሎች አሠራር፣ ሥያሜና ምሳሌነታቸውም መንፈሳዊ በመሆኑ ደርዳሪዎቹም ወደ መንፈሳዊ ሕይወት የሚመራም መንፈሳዊ መሣሪያ ነው።

በገና በሁለት አይነት መልኩ ይተረጎማል

ነ. ሰዋስዋዊ ትርጉም

አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ"መጽሐፈ ሰዋስው ወግሥ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ"

➢ ሲላላ፡-ነዘረ፣ መታ፣ ደረደረ፣ ማለት ነው።።

➢ ሲጠብቅ ፡- ነደደ፣ ተቆጣ... ያሰኛል ብለዋል።።

➢ በገና፡- በዕብራይስጥ "ናጌን" ይባላል።

➢ በገና በቁሙ መዝሙር ማለት ነው ብለውም ፈትተውታል።።ለዚህም ማስረጃ ቅዱሱ መጽሐፍ ነው። ግነዩ ለእግዚአብሔር በመሰንቆ ወበመዝሙር ዘአስርቱ አውታሪሁ። "እግዚአብሔርን በመሰንቆ አመስግኑት አሥር አውታር ባለው በበገና ዘምሩለት" መዝ.፴፪ ፴፫፡፪ "ወበመዝሙር" የሚለው በገናን ለመግለጽ ወይም ለማጠየቅ ነው፡

ከሳቴ ብርሃን ተሰማ "የአማርኛ መዝገበቃላት"

➢ በገና በአሥር አዉታር ጅማት በገናን ሠራ፣ቃኘ፣ ደረደረ፣ ድምጽን እያጣራ፣ እያጣቀሰ፣

እየነዘረ... በገናን በገነ... ካሉ በኋላ "በገነኛ" የሚለው ደግሞ በገናን የሚመታ፣ በገናን

የሚያውቅ ደርዳሪ... ማለት ነው ብለው ተርጉመውታል።

2. ሥነ ቃላዊ ትርጉም

➢ በገነ ማለት አደረቀ፣ አቃጠለ፣ አነደደ... ማለት ነው።። በገናም ከዚህ የሚወጣ ስም ነው፡

የዚህንም ትርጉም የበገና ሁለገብ ሰውነት በደረቅ ነገሮች ማለትም በደረቅ እንጨትና በደረቅ

ቆዳ እንዲሁም በደረቅ ጅማት የሚሠራ ወይም የሚዘጋጅ ስለሆነ በገና ተባለ ተብሎ

ይተረጐማል።

መምህር ሙሴ ኃይሉ

➢ በገነ ማለት ደረደረ ማለት ነው።። ስለሆነም በገና ማለት ድርደራ፣ ምስጋና፣ መዝሙር...

ማለትነው። ይህም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃ መሠረት በማድረግ ይተረጎማል።።

➢ በገና ምስጋና ማለት ነው። "አቤቱ አምላኬ በበገና አመሰግንሃለሁ"መዝ ፸፪÷፸፫-፩

➢ በገና ድርደራ ማለት ነው። "ለእግዚአብሔር በገና ደርድሩለት" መዝ ፸፮÷፩

➢ በገና መዝሙር ማለት ነው። "እግዚአብሔርን በመሰንቆ አመስግኑት አሥር አውታር ባለው

በበገና ዘምሩለት" መዝ ፴፪÷፴፫-፪

በገና በመጽሐፍ ቅዱስ

በገና ለመጀመሪያ ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰው በዘፍ. 4፥21 ሲሆን የላሜሕ ልጅ ዮህባል በገና እና መለከት ለሚይዙ አባት እንደሆነ ተጠቅሷል። ይህ ታሪክ ሌሎች በገና እና መለከትን የሚይዙ ሰዎች እንደነበሩና ዮባል አለቃቸው እንደነበረ ያስረዳል። ከዚያን ዘመን ጀምሮ በገና እግዚአብሔርን የማመስገኛ የዜማ ዕቃነቱ ታውቆ እንደሌሎቹ የቤተ መቅደስ የዜማ ዕቃዎች መለከት፣ መሰንቆ፣ ጸናጽል በሌዋውያን በተመረጡ አለቆች አማካኝነት አገልግሎት ይሰጥ ነበር።

- የእግዚአብሔር ታቦት ከአሚናዳብ ቤት ወደ አቢዳራ ቤት በገባ ጊዜ-

2ኛ ሳሙ. 6፥5 «ዳዊትና የእስራኤልም ቤት ሁሉ በቅኔና በበገና፣ በመሰንቆ፣ በከበሮም፣ በነጋሪትና በጸናጽል በእግዚአብሔር ፊት በሙሉ ኃይላቸው ይጫወቱ ነበር።»

- የእግዚአብሔር ታቦት ከአቢዳራ ቤት ወደ ዳዊት ከተማ በመጣች ጊዜ፡-

1ኛ ዜና 15፥16-24 «ዳዊትም በዜማ ዕቃ በመሰንቆና በበገና፣ በጸናጽልም እንዲያዜሙ ድምጻቸውንም በደስታ ከፍ እንዲያደርጉ መዘምራኑን ወንድሞቻቸውን ይሾሙ ዘንድ ለሌዋውያን አለቆች ተናገረ።»

1ኛ ዜና 15:21 «... ስምንት አውታር ባለው በገና ይዘምሩ ነበር።»

መዝ. 32፥2 «እግዚአብሔርንም በመሰንቆ አመስግኑት፤ ዐሥር አውታርም ባለው በገና ዘምሩለት።»

1ኛ ዜና 15፥28 «እስራኤል ሁሉ ሆ እያሉ ቀንደ መለከትና እምቢልታ እየነፉ ጸናጽልና መሰንቆም በገናም እየመቱ የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ታቦት አመጡ።»

የእግዚአብሔር ታቦት ከዳዊት ከተማ ሰሎሞን ወደ ሠራው ቤተመቅደስ ሲገባ፡-

2ኛ ዜና 5፥12-14 «መዘምራንም የነበሩት ሌዋውያን ሁሉ አሳፍና ኤማን ኤዶታምም ልጆቻቸውም ወንድሞቻቸውም ጥሩ በፍታ ለብሰው ጸናጽልና በገና መሰንቆም እየመቱ በመሰውያው አጠገብ በምሥራቅ በኩል ቆመው ነበር። ከእነርሱ ጋር መቶ ሃያ ካህናት መለከት ይነፉ ነበር። እግዚአብሔር ቸር ነውና ምሕረቱም ለዘላለም ነውና እግዚአብሔርን አመስግኑ እያሉ በአንድ ቃል ድምጻቸውን ወደ ላይ ከፍ አድርገው በመለከትና በጸናጽል በዜማም ዕቃ ሁሉ እግዚአብሔርን ባመሰገኑ ጊዜ ደመናው የእግዚአብሔርን ቤት ሞላው።»

እግዚአብሔር በጠላቶቻቸው ላይ ደስታን በሰጣቸው ጊዜ- 2ኛ ዜና 20፥27-28 «የይሁዳና የኢየሩሳሌም ሰዎች በፊታቸውም ኢዮሳፍጥ እግዚአብሔር በጠላቶቻቸው ላይ ደስ አሰኝቶአቸዋልና በደስታ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄዱ ዘንድ ተመለሱ። በበገናና በመሰንቆ በመለከትም ወደ ኢየሩሳሌም ወደ እግዚአብሔር ቤት ገቡ።»

ያዕቆብ ከላባ በኮበለለ ጊዜ ላባ ለያዕቆብ ሲናገረው፡- ዘፍ. 31፥27 «ስለምን በስውር ሸሸህ? ከእኔም ከድተህ ስለምን ኮበለልህ? በደስታና በዘፈን በከበሮና በበገና እንድሰድድህ ለምን አልነገርኸኝም?»

ከላይ _ በተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በገና እንደ ሌሎች የቤተ መቅደስ የዜማ ዕቃዎች የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት ከአቢዳራ ቤት በምትመጣበት ጊዜ፣ በዳዊትም ከተማ ገብታ በድንኳን በኖረችበት ጊዜ ሁሉ፣ ንጉሥ ሰሎሞን የእግዚአብሔርን ቤት ሠርቶ በጨረሰ ጊዜ፣ ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር በጠላቶቻቸው ላይ ድልን በሰጣቸው ጊዜ አገልግሎት ይሰጥ እንደነበረ ተገልጧል። በገና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ላይ አገልግሎቱ ቢጠቀስም በይበልጥ የታወቀውና አገልግሎቱ የሰፋው በቅዱስ ዳዊትና እርሱ በነበረበት ዘመን ነው።

ቅዱስ ዳዊት ከእግዚአብሔር ከተሰጡት ሰባት ሀብታት መካከል ሁለቱ ሀብተ በገና እና ሀብተ ፈውስ ናቸው።

ሀብተ በገና - አንጨት ጠርቦ፣ቁርበቱን ጎልቦ፣ጅማቱን ወጥሮ መደርደር ሲሆን፤

ሀብተ ፈውስ - በገናውን የደረደሩ ድውይ መፈወስ ነው። ይህስ ሀብተ በገና ካለው ይገባል ቢሉ ሀብተ ፈውስ መንፈሳዊ አመታት (ድርደራ) ነው። 1ኛ ሳሙ 16:14-23 (መዝሙረ ዳዊት አንድምታ መቅድም)

ቅዱስ ዳዊት በገና መልካም አድርጎ መምታት የሚችል ጽኑዕ፣ ኃያል በነገርም ብልህ መልኩም ያመረ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር የነበረ ብላቴና ነበር። ነቢዩ ሳሙኤል ከእሴይ ልጆች ቅብዓ ነገሥት ሊቀባ በሄደ ጊዜ እሴይ መልከ መልካሞቹን፣ ቁመታቸው ዘለግ ያለውን ሰባቱን ልጆቹን ለምርጫ አሳለፈ። ሁሉንም እግዚአብሔር አልመረጠም «ሰው ፊትን ያያል እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል።» አለው። እግዚአብሔር ትንሹ ብላቴና የበጎቹ ጠባቂ እረኛው ዳዊት ሲመጣ ነቢዩ ሳሙኤልን «ይህ ነውና ተነሥተህ ቅባው አለ፤ ሳሙኤልም የዘይቱን ቀንድ ወስዶ በወንድሞቹ መካከል ቀባው። የእግዚአብሔርም መንፈስ ከዚያን ቀን ጀምሮ በዳዊት ላይ በኃይል መጣ።» ይላል መጽሐፍ ቅዱስ። ከላይ እንዳየነው ቅዱስ፣ ንጉሥ ዳዊት ከብላቴናነቱ ጀምሮ በእግዚአብሔር የተመረጠና የተወደደ ስለነበረ በሰውም ዘንድ መልካምነቱ፣ በገናን ጥሩ አድርጎ መምታቱ የተመሰከረለት ነበር።

የእግዚአብሔር መንፈስ ከሳኦል ርቆ ክፉ መንፈስ ባሰቃየው ጊዜ የሳኦል ባሪያዎች በገና መልካም ተደርጎ ሲመታ ክፉ መንፈስ እንደሚርቅና የታመመውም እንደሚድን ያውቁና ያምኑ ስለነበረ ሳኦልን መክረውት እርሱም ሃሳባቸውን ተቀብሎ መልካም አድርጎ በገና መምታት የሚችል ሰው እንዲያመጡለት አዘዘ፡፡ ይህ ታሪክ በገና ሲደረደር ርኩስ መንፈስ እንደሚርቅና ብዙ በገና ደርዳሪዎች እንደነበሩ የሚያስረዳ ሲሆን ካሉት ውስጥ መልካም አድርጎ የሚመታው ሀብተ ፈውስ ያለው የቤተልሔማዊው የእሴይ ልጅ ቅዱስ ዳዊት እንደሆነ ታውቋል፡፡ 1ኛ ሳሙ. 16፥14 -23

በተለያየ ወቅት ንጉሥ ሳኦል ክፉ መንፈስ ባሰቃየው ጊዜ ቅዱስ ዳዊት በገና በእጁ እየመታ ሳኦልን ደስ ያሰኘው ከጭንቀትም ያሳርፈው ነበር፡፡ ክፉ መንፈስም ከሳኦል ይርቅ ነበር፡፡ ይህ ታሪክ ደግሞ በገና ሲደረደር ሰውን ደስ እንደሚያሰኝ፣ ከጭንቀትም እንደሚያሳርፍ፣ ክፉ መንፈስም እንደሚርቅ ያሳያል፡፡ 1ኛሳሙ.16፥14- 23

በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በገና በብዙ ቦታዎች ላይ የተጠቀሰ ሲሆን ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

ዘፍ 4፥20 ፤ ዘፍ 31፥27 ፤ 1ኛ ሳሙ 10፥5 ፤ 16 ፥ 14 - 23 ፤ 18፥6-9 ፤ 19፥10 ፤ 1ኛ ዜና 15፥21 ፤ 16፥6 ፤ 2ኛ ዜና 20፥28 ፤ መዝ 3 2፥2 ፤ 42፥4 ፤ 48፥4 ፤ 56፥8 ፤ 70፥2 ፤ 80 ፥2 ፤ 91፥3 ፤ 107፥2 ፤ 150፥3 ፤ 143፥9

በገና በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በብዛት ባይገለፅም የአዲስ ኪዳን የትንቢት መፅሐፍ በሆነው በዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ ውስጥ የበገና ሰማያዊ አገልግሎት ተገልጿል፡፡

ዮሐ. ራእይ 5፥8 «መጽሐፉንም በወሰደ ጊዜ አራቱ እንስሶችና ሃያ ዐራቱ ሽማግሌዎች በበጉ ፊት እያንዳንዳቸውም በገናና የቅዱሳን ጸሎት የሆነ ዕጣን የሞላበትን የወርቅ ዕቃ ያዙ::» ዮሐ. ራእይ 14፥2 «... ደርዳሪዎችም በገና እንደሚደረድሩ ያለ ድምፅ ሰማሁ።» ዮሐ. ራእይ 15 «በአውሬውና በምስሉም በስሙም ቁጥር ላይ ድል ነስተው የነበሩት የእግዚአብሔርን በገና ይዘው በብርጭቆ ባህር ላይ ሲቆሙ አየሁ::»

በገና ከብሉይ ኪዳን የመጀመሪያ መጽሐፍ ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ መጨረሻው የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ዮሐንስ ራእይ ድረስ አገልግሎቱ የተጠቀሰ ሲሆን በአጠቃላይ አገልግሎቱ ሲታይ በኅብረትም (በአለቃ) እና በግል (ለብቻ) ሆኖ አገልግሎት ሊሰጥ የሚችል የዜማ መሣሪያ እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡

በገና በመጽሐፍ ቅዱስ በተጠቀሰው ታሪኩ ስምንት አውታርና አሥር አውታር ያለው ሁለት ዓይነት በገና እንዳለ ተጠቅሷል፡፡ ቅዱስ ዳዊት ግን ይጠቀምበት የነበረው በገና አሥር አውታር ያለው እንደሆነ በመዝ 32፥2 ላይ ተጽፎ እናገኛለን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ቅዱስ፣ ንጉሥ ዳዊት ከእርሱም በፊት ከእርሱም በኋላ በበገና ደርዳሪነት ስሙ የገነነ የለም እንጂ ብዙ በገና ደርዳሪዎች በየዘመኑ እንደነበሩ ያስረዳል፡፡

በገና በኢትዮጵያ

ኢትዮጵያ በሕገ ልቡና እና በሕገ ኦሪት እግዚአብሔርን ታመልክ የነበረች ሀገር ስለነበረች ሕዝበ እግዚአብሔር ከሚባሉት ከእስራኤላውያን አንድ ዓይነት የአምልኮ ሥርዓት ነበራቸው፡፡ ሙሴ ኢትዮጵያዊት ሚስት ማግባቱ ኢትዮጵያውያን ከእስራኤላውያን ጋር በአምልኮ አንድ መሆናቸውን አስረጂ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ከአሕዛብ ጋር አይጋቡም ነበርና፡፡ «የእስራኤል ልጆች ሆይ፤ እናንተ ለእኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን?» ት. አሞጽ 97 በማለት እግዚአብሔር ለኢትዮጵያውያን ያለውን ፍቅር ገልጧል፡፡ ስለዚህ እስራኤልና ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ በአምልኮ ሥርዓታቸው አንድ ስለነበሩ ንግሥተ ሳባ የሰሎሞንን ጥበብ ለማየት ከመሄዷ በፊት በኢትዮጵያ በገና ነበር ተብሎ ይታመናል፡፡ ሙሴ የቃል ኪዳኑን ታቦት በሲና ተራራ ከእግዚአብሔር ከተቀበለ ጀምሮ በድንኳን ትኖር ነበር፤ እስራኤላውያንም በሙሴ እየተመሩ አምልኮታቸውን ይፈጽሙ ነበር፡፡ ቅዱስ ዳዊት በነገሠ ጊዜ መዘምራን በቃል ኪዳኑ ታቦት ፊት በዜማ ዕቃ በመሰንቆና በበገና በጸናጽልም እንዲያዜሙ ድምጻቸውንም በደስታ ከፍ እንዲያደርጉ መዘምራኑን ይሾሙ ዘንድ ለሌዋውያን አለቆች ትዕዛዝ አስተላለፈ /ተናገረ/፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በዜማ ዕቃ በመሰንቆ፤ በበገና፣ በጸናጽል በቃል ኪዳኑ ታቦት ፊት ዝማሬ ማቅረብ ሥርዓት ሆኖ ተሠራ፡፡

በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ ምዕራፍ 10 እንደተገለጠው ንግሥተ ሳባ በእግዚአብሔር ስም የወጣለትን የሰሎሞንን ዝና በሰማች ጊዜ ወደ እርሱ ሄዳ «አንተን የወደደ በእስራኤልም ዙፋን ያስቀመጠህ አምላክህ እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን፡» በማለት በዝና

የሰማችውን ሰሎሞንን ሳይሆን ለሰው ጥበብን ሥልጣንን ክብርን የሚሰጠውን እግዚአብሔርን አመሰገነች። በኢየሩሳልም ከንጉሥ ሰሎሞን ጋር በነበራት ቆይታ በፈቃደ እግዚአብሔር ቀዳማዊ ምኒልክን ፀንሳ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሳለች።

ቀዳማዊ ምኒልክ ኢትዮጵያ ተወልዶ አድጎ አባቱን ለማየት ኢየሩሳሌም ሄዶ ሲመለስ በፈቃደ እግዚአብሔር ታቦተ ጽዮንን፣ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን፣ የቤተመቅደስ መገልገያ ንዋያተ ቅድሳትን ከነሙሉ ሥርዓቱ በካህናትና በመኳንንት ታጅቦ በክብር ወደ ኢትዮጵያ እንደመጣ የታመነ ነው። ኢትዮጵያ ከመጀመሪያ የብሉይ ኪዳን እምነትን ትከተል ስለነበረ አዲስ ኪዳንን ስትቀበል በዘመነ ብሉይ ትፈጽማቸው የነበሩትን ሥርዓቶች የሚሻሩትን ሽራ፣ የሚሻሻሉትን አሻሽላ፣ ሙሉ ለሙሉ ተቀባይነት ያገኙትን ተቀብላ በአዲስ ኪዳንም እየተጠቀሙች ያለች አገር ናት። በአፄ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት በአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሳው ኢትዮጵያዊው ጻድቅ ማኅሌታይ ቅዱስ ያሬድና ከእርሱም በኋላ የተነሱት ቅዱሳን አባቶች ከበሮንና ጸናጽልን ከመዝሙር (ከዜማ) ጋር አስማምተው ለቤተክርስቲያን የውስጥ አገልግሎት እንዲውሉ አድርገዋል። ከቅዱስ ያሬድ በፊት ባለው ዘመን ለቤተክርስቲያን የዝማሬ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ የዜማ ዕቃዎች እያሉ ለቤተክርስቲያን የውስጥ አገልግሎት ከዜማ ጋር ያስማማቸው ስላልነበረ አሁን እየሰጡ ያሉትን አገልግሎት አይሰጡም ነበር። የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ለቅዱስ ያሬድ ምሥጢሩን ከገለጠለት በኋላ ለቤተክርስቲያን የውስጥ አገልግሎት ውለዋል።

በገና ከዚያን ዘመን በኋላም እግዚአብሔርን በማመስገኛ መሣሪያነቱ በክብር በቤተክህነትና በቤተ መንግሥት ሥልጣን ባላቸው በነገሥታቱና በመኳንንቱ ቤት አገልግሎት ይሰጥ ነበረ። ከኢትዮጵያ ነገሥታትም አፄ ቴዎድሮስ፣ አፄ ዮሐንስ፣ አፄ ምኒልክ፣ እቴጌ ጣይቱ፣ ራስ መኮንን (የአፄ ኃ/ሥላሴ አባት) በገና ደርዳሪዎች እንደነበሩ ሌሎችም ነገሥታትና መኳንንት በገና ይደረድሩ እንደነበረና መደርደር ባይችሉ እንኳን በገና ደርዳሪ እንደነበራቸው ይነገራል። በተለይ በቤተክርስቲያናችን ብዙ ጠቃሚ መንፈሳዊ መጽሐፍትን በመጻፍ ታሪካቸውን በቅርብ የምናውቀው ሊቁ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀምበሬ በ1914 ዓ.ም ጽፈው በ1922 ዓ.ም በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ለሕትመት ያበቁት «የበገና መዝሙር ምሥጢረ ሃይማኖት ዘይነግር» በሚል ርዕስ የባለ በገናዎችን መንፈስ በድርሰት ለመደገፍ ብለው የጻፉት የመዝሙር መጽሐፍ በወቅቱ ብዙ በገና ደርዳሪዎች እንደነበሩ ያስገነዝባል። አሁንም እድሜ ጠገብ አዛውንቶች እንደሚናገሩት በዘመናቸው በገና ደርዳሪዎች እንደነበሩ፤ በተለይ በመኳንንቱ አካባቢ የቤት እመቤቶች በገና እንዲደረድሩ፣ ዳዊት እንዲደግሙ ይበረታቱ እንደነበረ፤ በገዳማትም በገና የሚደረድሩ አባቶች እንደነበሩ፤ በገና የሚደረደረውም በብዛት በዐቢይ ጾም፣ ዘወትር ቅዳሜ ማታ የሰንበት እሳት እያነደዱ ሌሊቱን፣ በሌላም ቀን ማታና ሌሊት፣ በኀዘንና በትካዜ ጊዜ እንደነበር ይናገራሉ። በአጠቃላይ የበገናን ታሪክ ስናይ ከብሉይ ኪዳን ጀምሮ አገልግሎቱ አንድ ዘመን ሲገለጥ (ሲነላ) በሌላ ዘመን ሲረሳ በእግዚአብሔር ፈቃድ እዚህ ዘመን ደርሶ ከ1966 ዓ.ም በኋላ የበገና ደርዳሪዎች ቁጥር እየቀነሰና በዐቢይ ጾም በሬዲዮ የበገና ዜማ በየቤቱ መደመጡ ቀርቶ ለመጥፋት የተቃረበ ቢመስልም በእግዚአብሔር ቸርነት በወቅቱ የነበሩት በገና ደርዳሪዎች በየቤታቸውም ቢሆን እየደረደሩ ያቆዩት ሲሆን በተለይ ታዋቂው የበገና ደርዳሪ መጋቤ ስብሐት ዓለሙ አጋ በያሬድ የሙዚቃ ት/ቤት በማስተማር፣ ከዚያም ከወጡ በኋላ በገናን መማር ለሚፈልግ ሁሉ በነፃ በማስተማር፣ በገናን በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር ባገኙት መድረኮች ሁሉ መንፈሳዊ ይዘቱን ሳይለቅ ታሪኩን ክብሩን ለመንፈሳዊ አገልግሎት ብቻ የሚውል የቤተክርስቲያናችን መንፈሳዊ የዜማ መሣሪያ መሆኑን በማስተዋወቅ ታላቅ መንፈሳዊ አስተዋጽኦ አበርክተዋል።

በገና አሁን ከቅርብ ዓመታት በኋላ አገልግሎቱ እየጨመረ በመሄዱ በገና የመደርደር ፍላጎት ያላቸው ሰዎች ቁጥር እየጨመረ መጥቷል። በገና ደርዳሪዎችም እንደ አቅማቸው መማር ለሚፈልጉ ሰዎች በገናን እያስተማሩ ሲሆን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን በ1996 . (ሐምሌ) በከፈተው «አቡነ ጎርጎርዮስ የአብነትና የዜማ ትምህርት ማዕከል» ከ300 በላይ ተማሪዎችን ያስተማረ ሲሆን ይህ መጽሐፍ ለሕትመት በተዘጋጀበት ዓመት ማለትም መጋቢት 2003 ዓ.ም 185 ተማሪዎችን አስመርቋል። ትምህርት ቤቱ እስከአሁን ካስተማራቸው ተማሪዎች ውስጥ አራት የበገና መምህራንን ያፈራ ሲሆን የተመረቁ ተማሪዎች ተበትነው እንዳይቀሩ በግልም ሆነ በሕብረት እንዲያገለግሉና ሁሉንም የበገና ደርዳሪዎችን ለማሰባሰብ እንዲቻል «የቅዱስ ዳዊት የበገና ቤተሰብ» ኅዳር 26 ቀን 2003 ዓ.ም ተመሥርቶ አገልግሎቱን እያጠናከረ ይገኛል።

እንዲሁም በጉራጌ ዞን በምሁር ገዳመ ኢየሱስ በእግዚአብሔር ቸርነት፤ በገዳሙ አስተዳደር በጎ ፈቃድና ቀና ትብብር፣ በበጎ አድራጊዎች ድጋፍ በገዳሙ ለሚኖሩ መነኰሳት፤ መናንያን፣ የአብነት መምህራንና ተማሪዎች ከየካቲት 16 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ የበገና ድርደራ ትምህርት እየተሰጠ ተማሪዎችም በትምህርት አቀባበላቸው አበረታች ውጤት በማሳየት ለጸሎትና ለምስጋና እየተጠቀሙበትና ለሌሎች መናንያንና መነኰሳት እንዲሁም በገዳሙ በሱባኤ ለሚሰነብቱ ምዕመናን እያስተማሩ

ይገኛሉ። በገና ለመንፈሣዊ አገልግሎት ብቻ የሚውል የቤተክርስቲያናችን የዜማ ዕቃ መሆኑን አውቀን እንደ ግለሰቦች አቅምና ፍላጎት ተወስኖ እንዳይቀር መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪኩን፣ክብሩን፣ መንፈሳዊ ጥቅሙንና አጠቃቀሙን ተረድተን በአጽዋማት ጊዜ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ቀናት በቤተክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት የሚሰጥበት ሥርዓት ሊሠራለትና በግላችንም ለጸሎትና ለተመስጦ የመጠቀም ልምዳችንን ልናዳብር ይገባል። ይህ ዘመናትን ተሻግሮ በፈቃደ እግዚአብሔር በእጃችን የገባውን የዜማ ዕቃ በገናን በትምህርት ቤትም ሆነ በቤታችን ስንይዘውም ሆነ ስንጠቀምበት በሥርዓትና በጥንቃቄ ሊሆን ይገባል። እግዚአብሔር በዚህ ጭንቀት፣ ሐዘንና መከራ በበዛበት ዘመን በገናን ያስነሳበት የራሱ ዓላማ አለውና መልካም አድርጎ በገና መደርደር (ሀብተ በገና)፤ በገና እየደረደሩ መፈወስ (ሀብተ ፈውስ) ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ስጦታ መሆኑን አምነን ስጦታውን ለራስ ክብር ሳይሆን ለእግዚአብሔር ክብር እና ለቤተክርስቲያን ጥቅም በፍቅር ልንጠቀምበት ይገባል።

« የሰማይ አምላክ ያከናውንልናል እኛም ባሪያዎቹ ተነስተን እንሠራለን።» ነህ. 2፥20

የበገና ዓይነቶች

በገና በመጽሐፍ ቅዱስ ዓይነቱና ቅርጹ በውል ባይታወቅም ስምንት አውታርና አሥር አውታር ያላቸው በገናዎች እንደነበሩ ያስረዳል። ፤ኛዜና. 15፥21፣ መዝ. 32፥2፣ 91፥3፣ 143፥9

በመጽሐፍ ቅዱስ ከኦሪት ዘፍጥረት ጀምሮ የዜማ ዕቃዎች አገልግሎት የተጠቀሰ ሲሆን በጥንት ጊዜ ሦስት ዓይነት የዜማ ዕቃዎች እንደነበሩ ተጠቅሰዋል። ይኸውም፡-

1. አውታር ያለው የዜማ ዕቃ፡- ዘማሪው በእጅ ወይም በመከርከሪያ ሲመታው ድምጽ ይሰጣል። በገና፣ ክራርና መሰንቆ ከባለ አውታር የዜማ ዕቃ ከፍል ናቸው።

2. የሚነፋ የዜማ ዕቃ፡- በዚህ ዓይነት የዜማ ዕቃ ውስጥ መለከት፣ እምቢልታና ዋሽንት ተጠቅሰዋል።

3. ዕቃዎችን እርስ በርስ በማማታት ወይም በእጅ በኃይል በመምታት የሚጠቀሙባቸው ዕቃዎች- እነዚህም ከበሮ፣ አታሞ፣ ነጋሪትና ጸናጽል ናቸው። (የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት - የዜማ ዕቃ)

በዘመናዊ ሙዚቃ ውስጥ የዜማ መሣሪያዎችን በአምስት ምድብ ይከፍላቸዋል። እኒህም፡-

1. እርስ በርስ በመጋጨት ድምጽ የሚሰጡ (Ideophone)

2. የከር (አውታር) መሣሪያዎች (Chordaphone)

3. ለመምታት ታስበው በቆዳ ወይም በሌላ ነገር የተሸፈኑ የዜማ ዕቃዎች (Membraphone)

4. የትንፋሽ መሣሪያዎች (Aerophone)

5. በኤሌትሪክ አማካኝነት ድምጽ የሚፈጥሩ መሣሪያዎች (Electrophone)

ከላይ በተጠቀሰው የዜማ መሣሪያዎች አመዳደብ መሠረት በገና አውታር ካላቸው የዜማ ዕቃዎች (Chordaphone) የሚመደብ ሲሆን በእድሜው ትልቅነትም ለአውታር መሣሪያዎች አባት ሊባል የሚችል ነው።

በዓለማችን ላይ በተለያዩ አገሮች በገና ወይም ሀርፕ የሚባል የዜማ መሣሪያ ቢኖርም እንደየአገሩ ሁኔታ ቅርጹና የክሩ (አውታሩ) ቁጥር የተለያየ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው በገና ትክክለኛው በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰው እንደሆነ ይታመናል። ይኸውም፡-

1. ቅዱስ ዳዊት አሥር አውታር ባለው በገና እዘምርልሃለሁ ባለው መሠረት አሥር አውታር ስላለው፣

2. ኢትዮጵያ የእግዚአብሔር የምሥጢር አገሩ ስለሆነች በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ይመሰገንባቸው የነበሩት የዜማ ዕቃዎች እንደ መሰንቆ፣ ከበሮ፣ ጸናጽል፣ መለከትና የመሳሰሉት ለቤተመቅደስ አገልግሎት የሚውሉት ንዋያተ ቅድሳት ቅርፃቸው ሳይለወጥ መኖራቸው፣

3. በገና በታቦተ ጽዮን ፊት አገልግሎት ይሰጥ ስለነበር እና ታቦተ ጽዮንም በፈቃደ እግዚአብሔር በንጉሥ ሰሎሞን ልጅ በዳዊት (ምኒልክ) ዘመን ወደ ኢትዮጵያ መጥታ በሀገራችን መኖሯ፣ (ክብረ ነገሥት መጽሐፍ የንጉሥ ሰሎሞንን ልጅ ምኒልክን ዳዊት ይለዋል።)

4. በኢትዮጵያውያን ባህል ለቤተክርስቲያንና ለቤተመንግሥት ዕቃዎች ልዩ ክብር ስለሚሰጥ በገና በቤተክርስቲያንም በቤተመንግሥትም አገልግሎት የሚሰጥ ስለሆነና ስለነበረ ቅርጹና ይዘቱን ሳይለቅ የመኖር እድል በማግኘቱ፣

5. ሌሎች በገና ይኖርባቸዋል የሚባሉት አገሮች እንደ ኢትዮጵያ በሕገ ልቡና እና በሕገ ኦሪት እግዚአብሔርን ያመልኩ ስላልነበረ የብሉይ ኪዳን የዜማ ዕቃዎች ይኖራቸዋል ተብሎ አይታሰብም። በመሆኑም በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው በገና በመጠን፣ በቀለምና በላያቸው ላይ በሚደረጉ ጌጣጌጦች (ቅርጻ ቅርጾች) ይለያዩ እንጂ ሁሉም አንድ ቀንበር፣ ሁለት የግራና የቀኝ ምሰሶዎች፣ አንድ ገበቴ (የድምጽ ሳጥን)፣ አንድ ብርኩማ፣ አንድ መወጠሪያ፣ አሥር አውታር፣ አሥር እንዚራ፣ አሥር መቃኛ አላቸው።

የበገና አካል ክፍሎች እና



❖ ቀንበር

ቀንበር ከበገና ከላይኛው ክፍል የሚገኝ አግዳሚ ሲሆን ቀጥ ያለ ወይም የቀንደ መለከት ቅርጽ ሊኖረው ይችላል። አውታሩ የሚወጠርበት እና መቃኛው የሚያርፍበት ክፍል ነው። የሚሠራውም ከደረቅ እንጨት ተጠርቦ እና ለዜቦ እንዲሁም በልዩ ጥበብ ተውቦ ነው።

ምስጢሩ፦

- ቀንበር የአጎዜ ኩሉ እግዚአብሔር ምሳሌ ነው።
- ቀንበር ከበገናው በላይ መገኘቱም፦ አምላካችን ቅዱስ እግዚአብሔር በላይ በሰማይ ያለ ሁሉን የፈጠረ፣ሁሉን የሚያስተዳድር ጌታ፣የሁሉ የበላይ መሆኑን ያጠይቃል።
- አንድም የሥልጣነ የእግዚአብሔር ምሳሌ ነው።
- አንድም የእግዚአብሔርን ልዕልና ያመለክታል።

❖ ጌጥ (መስቀል፣ቀርነ በግዕ)

መስቀል፦ እግዙአብሔር ስለ ሰው ልጆች ፍጹም ፍቅሩን የገለጠበት ነው።

ቀርነ በግዕ፦የበግ ቀንድ ማለት ነው።በብሉይ ኪዳን የተለያዩ ንዋያተ ቅድሳት ከቀንድ ይሠሩ ነበር። ለምሳሌ ቀርነ ቅብዕ/የዘይት መያዣ(1ኛ ሳሙ.16፣1) በተጨማሪም ቀንደ መለከት(ኢያ.6፣5)

በመጽሐፍ ቅዱስ ቀንድ ኃይልን፣ ሥልጣንን፣ ክብርን፣ ንግሥናን ያመለክታል።

በግዕ(በግ)

በግ በየዋህነቱ የሚጠቀስ የቤት እንስሳ ሲሆን በብሉይ ኪዳን ለመሥዋዕት ከሚሆኑ እንስሳት ዋነኛውና በተለይም በፋሲካ የሚሠዋ እንስሳ ነው። በቅዱሳት መጻሕፍት በግ የክርስቶስ ምሳሌ ሆኖ ተጠቅሷል። ምዕመናንም በበጎች ተመስለዋል።

በግ በመጽሐፍ ቅዱስ ፡-እስራኤል ከግብጽ በወጡበት ቀን የሠዉት የፋሲካው በግ (ዘጸ.12፣3-ፍጻሜ) ይህ በግ የክርስቶስ ምሳሌ እንደሆነ ንዋይ ጎሩይ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በ ፩ኛ ቆሮ.5፣7-8 ላይ "...እንግዲህ ያለ እርሾ እንዳላችሁ አዲሱን ሊጥ ትሆኑ ዘንድ አሮጌውን እርሾ አስወግዱ። ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዶአልና፤ስለዚህ በቅንነትና በእውነት ቂጣ በዓልን እናድርግ እንጂ በአሮጌ እርሾ በክፋትና በግፍ እርሾም አይደለም።" ብሎ ገልጦ አብራርቶታል። በተጨማሪም በይስሐቅ ፋንታ የተሠዋው "እግዙአብሔር ያዘጋጀው በግ" ። አብርሃም ልጅህን ሠዋልኝ ብሎ እግዙአብሔር የጠየቀውን ጥያቄ ለመፈጸም ልጁንና ለመሥዋዕት የሚሆነውን እንጨት ይዝ ከልጁ ከይስሐቅ ጋር እግዙአብሔር ወደ አዘዘው ስፍራ ለመሄድ ተነሳ፤አብርሃምም የመሥዋዕቱን እንጨት አንሥቶ ለልጁ ለይስሐቅ አሸከመው፤ እርሱም እሳቱንና ቢላዋውን በእጁ ያዘ፥ ሁለቱም አብረው ሄዱ። ይስሐቅም አባቱን አብርሃምን ተናገረው። አባቴ ሆይ? አለ እርሱም እነሆኝ ልጄ አለው። እሳቱና እንጨቱ ይኸው አለ፤ የመሥዋዕቱ በግ ግን ወዴት ነው?" አለው።(ዘፍ22፣6-7) አብርሃምም ልጄ ሆይ የመሥዋዕቱን በግ እግዙአብሔር ያዘጋጃል አለው፤ ሁለቱም አብረው ሄዱ።"(ዘፍ.22፣8) እንዳለውም እግዙአብሔር በግን አዘጋጀ። ይህ በግ የአማናዊው በግ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው። ይህንንም የሐዲስ ኪዳኑ ነቢይ የብሉዩ ሐዋርያ መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ብላቴናው ይስሐቅ ከሺህ ዓመታት በፊት "የመሥዋዕቱ በግ ወዴት ነው?" ብሎ የጠየቀውን ጥያቄ በሐዲስ ኪዳን "ነዋ በግዑ ለእግዙአብሔር ዘአትት ወያሴስል ኃጢአት ዓለም። "እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዙአብሔር በግ እነሆ የእግዙአብሔር በግ አለ።"ብሎ መልሶለታል።(ዮሐ.1፣29፣1፣36) ስለዚህ በግ የክርስቶስ ምሳሌ ነው።

ቀርን(ቀንድ)

የኃይለ እግዚአብሔር፣ የሥልጣነ እግዚአብሔር፣ የመስቀል ምሳሌ ነው። ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት ከአንድ ሺህ ዓመት በፊት በትንቢት መነጽር ዓይቶ ታላቅ ምሥጢር እንዲህ ሲል እንደተናገረው "...እስመ ኃረያ እግዚአብሔር ለጽዮን...ወበህየ አበቍኍል ቀርነ ለዳዊት ወአስተዴሉ ማኅቶተ ለመሲሕየ ወአለብሰሙ ኃፍረተ ለጸላእቱ ወበቱ ይፈረ ቅድሳትዩ። " ትርጉሙም "እግዚአብሔርጽዮንን መርጦአታልና፥ ማደሪያውም ትሆነው ዘንድ ወድዶአታልና፥ እንዲህ ብሎ "ይህች ለዘላለም ማረፊያዬ ናት፤ መርጫታለሁና በዚህች አድራለሁ፤ አሮጊቶችዋን እጅግ እባርካለሁ፥ ድሆችዋንም እንጀራ አጠግባለሁ፤ካህናቶችዋንም

ደኅንነትን አለብሳቸዋለሁ፥ ቅዱሳኖችዋም እጅግ ደስ ይላቸዋል፤በዚያ ለዳዊት ቀንድን አበቅላለሁ፥ ለቀባሁትም ሰው መብራትን አዘጋጃለሁ። ጠላቶችንም እፍረትን እለብሳቸዋለሁ፤ በእርሱ ግን ቅድስናዬ ያብባል።"(መዝ.131 ፥ 1-ፍጻሜ) ትርጉሙም፦ "እግዚአብሔር ጽዮንን መርጦአታልና፥ ማደሪያውም ትሆነው ዘንድ ወድዶአታልና፥ እንዲህ ብሎ። ይህች ለዘላለም ማረፊያዬ ናት፤ መርጫታለሁና በዚህች አድራለሁ፤ አሮጊቶችዋን እጅግ እባርካለሁ፥ ድሆችዋንም እንጀራ አጠግባለሁ፤ ካህናቶችዋንም ደኅንነትን አለብሳቸዋለሁ፣ ቅዱሳኖችዋም እጅግ ደስ ይላቸዋል።" ያለው ስለ እመቤታችን ሲሆን "በዚያ ለዳዊት ቀንድን አበቅላለሁ፥ ለቀባሁትም ሰው መብራትን አዘጋጃለሁ። ጠላቶችንም እፍረትን አለብሳቸዋለሁ፤ በእርሱ ግን ቅድስናዬ ያብባል" ያለው ደግሞ ስለ ጌታ፣ ስላለው ኃይልና ሥልጣን እንደሆነ ግልጽ ነው። ሲጠቃለልም ቀርነ በግዕ፡-የኃይለ እግዚአብሔር፣ የሥልጣነ እግዚአብሔር እንድም የመስቀል ምሳሌ ነው። ኃይለ እግዚአብሔርም ሥልጣነ እግዚአብሔርም የሚገለጠው/የተገለጠው በዙፋኑ በመስቀል ነውና በመስቀል ይጠቃለል።

❖ መቃኛ

ከቀንጫጭን ጠንካራ እንጨቶች የሚሠራ ሲሆን አወታሩን ቀንበሩ ላይ አሥሮ ይይዛል። አስተሳሰሩም የራሱ ብልሃት ያለው ነው።ለመቃኘት አውታሮቹን ለማጥበቅና ለማላላት እንዲረዳ ተደርጎ ይታሠራል።

ምስጢሩ፡-

- መቃኛ በመንፈስ ቅዱስ ይመሰላል። ሕግጋትን በመስጠት የምዕመናን ሕይወት የሚጠብቅ እርሱ ነውና። አንድም ዐሥሩ ትዕዛዛት መንፈሳውያን የሚያደርጉ የመንፈስንም ፍሬ የሚሰጡ በመሆናቸው ነው።
- ምድራዊ ሕይወታቸውን በቅድስና፣ በሰማዕትነት አሸንፈው ወይም ይህን ዓለም ድል ነስተው ወደ አሸናፊዋ ሰማያዊቷ ቤተ-ክርስቲያን አካል በተቀላቀሉ ዳሰንና ጻድቃን ሰማዕታት ይመሰላል።
- መቃኛ የመላእክት ምሳሌ ነው።

❖ ምሰሶ

በግራ በቀኝ የሚገኝ ቋሚ እንጨት ሲሆን፤ የሚሠራውም ልክ እንደ ቀንበሩ ከእንጨት ተጠርቦና ለዝቦ እንዲሁም በልዩ ጥበብ ተውቦና አጊጦ ነው።

ምስጢሩ፡-

- የቀኝ ምሰሶ፡-
- የፍቅረ እግዚአብሔር ምሳሌ ነው።
- የብሉይ ኪዳን ምሳሌ ነው
- የመጋቤ ብሉይ የቅዱስ ሚካኤል ምሳሌ ነው።

የግራ ምሰሶ፡-

- የፍቅረ ቢጽ (ሰው) ምሳሌ ነው።
- የሐዲስ ኪዳን ምሳሌ ነው።
- የመጋቤ ሐዲስ የቅዱስ ገበርኤል ምሳሌ ነው።

ሁለቱ ምሰሶዎች የግራ እና የቀኝ ምሰሶ በአንድ ቀንበር መያያዛቸው አንዳች ትምህርት የያዘ ነው። ይህም "ፍቅረ እግዚአብሔርን እና ፍቅረ ቢጽን (ቀኝ ምሰሶ እና ግራ ምሰሶ) አንድ ላይ ብንጠቀልላቸው ፍቅርየሚልን ትርጉም ይሰጡናል፤ ፍቅር ደግሞ በበገናው ቀንበር የተመሰለው አኀዜ ኵሉ እግዚአብሔር ነው።

❖ አውታር

ከበግ አንጀት ወይም ከበሬ ጅማት ታጥቦና ተልጎ፣ተገመዶ፣ተወጥሮ፣ከሮ፣በግኖና ደርቆ በቁጥርተቀምሮ ይሠራል።

ምስጢሩ፡-

- የበገና አውታሮች የአስርቱ ትዕዛዛት ምሳሌ ነው። ዘፀ 20፡1-17

1)ከኔ በቀር ሌሎች አማልክት አታምልክ፣

2)የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ አትጥራ፣

3)የሰንበትን ቀን አክብር፣

4)አባትህንና እናትህን አክብር፣

5)አትግደል፣

6)አታመንዝር፣

7)አትስረቅ፣

8)በሐሰት አትመስክር፣

9)የባልንጀራህን ገንዘብ አትመኝ፣

10)ባልንጀራህን አንደ ራስህ ውደድ፣

- የበገና አውታሮች በጽላቱ ወይም በታቦቱ ላይ የሚጻፉ አልፋ፣ ወዖ፣ ቤጣ፣ የውጣ የሚባሉት ኅቡዕ ቃላቶች ይመሰላሉ። ትርጉማቸውም አልፋ ምስራቅ፤ ወዖ ምዕራብ፤ ቤጣ ሰሜን፤የውጣ ደቡብ ማለት ነው። እንዲሁም ደግሞ እያንዳንዷ በገና አውታር ስም በመሆን በቁጥር እና በፊደል ለየብቻ ሲተነተኑ፡- 1አ ፣ 2ል፣ 3ፋ፣ 4ወ፣ 5ዖ፣ 6ቤ፣ 7ጣ፣ 8የ፣ 9ው፣ 10ጣ ይሆናሉ። እንዲሁም በፊደላት ብቻ የበገናው አውታሮች ስም በመሆን አ፣ ል፣ ፋ፣ ወ፣ ዖ፣ ቤ፣ ጣ፣ የ፣ ው፣ ጣ ናቸው።
- የበገና አውታሮች በሶስቱ ዓይነት የቅዱስ ያሬድ የዜማ ስልቶች (ድምጸ ዜማ) ይመሰላሉ። እነዚህም ግዕዝ፣ አራራይ፣ እዝል ሲሆኑ በእያንዳንዷ የበገና አውታር ይወከላሉ።በቁጥር እና በፊደል ሲተነተኑ፡- 1ግ፣ 2ዕ፣ 3ዝ፣ 4አ፣ 5ራ፣ 6ራ፣ 7ይ፣ 8እ፣ 9ዝ፣ 10ል ይሆናል። በፊደላት ብቻ ያለ ቁጥር ሲጻፍ ግ፣ ዕ፣ ዝ፣ አ፣ ራ፣ ራ፣ ይ፣ እ፣ ዝ፣ ል ናቸው
  ትርጉማቸው ግእዝ በአብ፣ አራራይ በመንፈስ ቅዱስ፣ ዕዝል በወልድ
- የበገና አውታሮች በበራሪ 3 ዓይነት ወፎች (ለቅዱስ ያሬድ ድምጸ ዜማን ባቀበሉት) ይመሰላሉ።
  ድምጸ ዜማዎቹ ግእዝ፣ ዕዝል፣ አራራይ ብቻ ሲሆኑ ዕዝል የመጣው ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ ሆኖ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከተወለደ በኋላ በቅዱስ ያሬድ ጊዜ ነው። በዚህ ምክንያት ዕዝል ከላይ የስም ተራውን ሳይጠብቅ መንፈስ ቅዱስን አልፎ በወልድ የተሰየመው በማለት ሊቃውንት ያስረዳሉ።
- አንድም በዐሥሩ የስሜት ሕዋሳት ይመሰላል።
- እንድም፡- በአስሩ የስሜት ሕዋሳት ይመሰላል። ለምሳሌ፡- ግነዩ ለእግዚአብሔር በመሰንቆ ወበመዝሙር ዘአስርቱ አውታሪሁ፡ "እግዚአብሔርን በመሰንቆ አመስግኑት አሥር አውታር ባለው በበገና ዘምሩለት" መዝ.32/33፡2

አስሩ የስሜት ሕዋሳት

አፍንጫ
ጆሮ
ምላስ እና አንደበት
ብልት
ሁለት አይን
ሁለት እጅ
ሁለት እግር



ወበመዝሙር ዘአስርቱ አውታሪሁ፡ አስር አውታር ያለውን በገና እየደረደራችሁ ተገዙ $ 3:16

አንድም አስር ሕዋሳት ባለው ሰውነት ምግባር ይዛችሁ ተገዙ። አንድም ሕግጋቱ አስር በሚሆኑ በአሪት ጸንታችሁ በመዓልትም በሌሊትም ተገዙ። አንድም ወበስብሐተ ሐዲስ ቃል ስጋ ሆነ እያላችሁ አመስግኑ

- የበገና አውታሮች በቅዱስ ዳዊት መዝሙር አርዕስት ይመሰላሉ፡
  ለቅዱስ ዳዊት ከተሰጠት ሀብቶች መሐከል ሀብተ ትንቢት ነው። ይህም ማለት 150ውን መዝሙሮች አስተካክሎ ለጸሎት ለምስጋና ማቅረቡ ነው። ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት 150ውን መዝሙሮች በአስር አርዕስት ከፋፍሎ አስቀምጧል። እነዚህም፡-
  - ተግሳጽ ለኩሎ- ብጹዕ ብእሲ
  - ትንቢት በእንተ ክርስቶስ፡- ለምንት እንገለጉ አሕዛብ
  - ትንቢት በእንተ ርዕሱ፡- እግዚኦ ሚ በዝነ
  - ትንቢት በእንተ መነናዊያን፡- ሶበ ጸዋእክዎ
  - ትንቢት በእንተ ትሩፋት፡- ቃልየ ኣፀምዕ እገዚኦ
  - ትንቢት በእንተ ሕዝቅያስ- ግብል አብድ በልቡ
  - ትንቢት በእንተ ኤርምያስ፡- ግፍዖሙ እግዚኦ ለእለ ይገፉእኒ
  - ትንቢት በእንተ መቃብያን- እግዚኦ ሰማእኮ በዕዘኒነ
  - ትንቢት በእንተ ዘለፋ ካህናት፡- አምላከ አማልክት እግዚኦብሔር ነበበ
  - ትንቢት በእንተ ሶሎሞን ወልዱ፡- እግዚኦ
- የበገና አውታሮች በአስሩ የቅዱሳን ማዕረጋት ይመሰላሉ

አስር ቁጥር በዕብራውያን የፍጹምነት መገለጫ በመሆኑ ፍጹምነት ደረጃ መድረሳቸውን ለመግለጥ አንድም አስርቱን ሕግጋቱን በመፈጸም የሚገኝ በመሆኑ አንድም በአስርቱ የስሜት ህዋሳት ንጹህነት የሚገኝ በመሆኑ።

አሥሩ የቅዱሳን ማዕረጋት ክፍሎች

1. ንጽሐ ሥጋ፡- ወጣንያን ናቸው ባለ ሰላሳ(30) ፍሬ ይባላሉ። በውስጡ ሶስት ማዕረጋት ይገኛሉ።

   ➢ ጽማዌ፡- ዝምታ ወይም አውቆ ፈቅዶ በመናገርና በመቀባጠር ከሚመጣው ኃጢአት መቆጠብ ማለት ነው

   ➢ ልባዌ ፡-ልብ ማድረግ ማልለትማት ነው

   ➢ ጣዕመ ዝማሬ፡- ሳይሰልቹና ሳይቸኩሉ ምሥጢርና ትርጓሜውን እያወጡ እያወረዱ በንቁ ሕሊና ማመስገንና መጸለይ ማለት ነው

2. ንጽሐ ነፍስ- ማዕከላዊያን ናቸው ባለ ስልሳ(60) ፍሬ ይባላሉ። በውስጡ አራት ማዕረጋት ይገኛሉ።

   ➢ አንብዕ፡- ስለ ራስ ኃጢአት ማልቀስ፣ስለ ወገን ማንባት፣ የጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጽዋትወ መከራ እያሰቡ፤በእመቤታችን ላይ የደረሰውን አምስቱ ሀዘናትን እያሰቡ ማዘን ማለት ነው

   ➢ ሑሰት፡-ባሉበት ስፍራ ሆነው ሌላ ቦታ የሚደረገውን ነገር ማወቅ ማለት ነው

   ➢ ኩነኔ ሥጋን ለነፍስ ማስገዛት ማለት ነው

   ➢ ፍቅር: -ሰውን ሁሉ በአንድ ዐይን መመልከት ማለት ነው

3. ንጽሐ ልቦና፡- ፍጹማን ናቸው ባለ መቶ(100) ፍሬ ይባላሉ። በውስጡ ሶስት ማዕረጋት ይገኛሉ።

   ➢ ንጻሬ መላእክት፡- ቅዱሳን መላእክትን በዐይነ ሥጋ መመልከት ማለት ነው

   ➢ ተሰጥሞ ብርሃን፡- እግዚአብሔር የባሕርይ ገንዘቡ በሆነው በሚያስደንቀው ብርሃን ውስጥ መዋኘት ማለት ነው

   ➢ ነጽሮተ ሥሉስ ቅዱስ(ከዊነ እሳት)፡- ሰውነት ለኢጋንንት የሚያቃጥልና የማያስቀርብ መሆን ማለት ነው

- የበገና አውታሮች የአስርቱ ዓለመ መላእክት(ከተሞች)ይመሰላል

➢ በኤረር ሶስት ከተሞች

➢ በራማ ሶስት ከተሞች

➢ በእዮር ሰስት ከተሞች

➢ እየሩሳሌም ሰማያዊት

- የበገና አውታሮች በቅዱስ ያሬድ ዐሥሩ የዜማ ምልክቶች ይመሰላሉ።

እነዚህም፡-ድፋት፣ሂደት ቅናት፣ ይዘት፣ቁርጥ፣ጭረት፣ርክርክ፣ደረት፣ድርስ፣አንበር ይባላሉ።

የበገና አውታሮች 12 ቢሆኑ ለሚሉ መላምቶች

1. በአብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይመሰላሉ።
2. በቅድስት ድንግል ማርያም ይመሰላሉ።
3. የ12ቱ ሊቃነ መላእክት ምሳሌነው።
4. የ12ቱ ደቂቀ ያዕቆብ(ነገደ እሥራኤል) ምሳሌ ነው።
5. የ12ቱ ቅዱሳን ሐዋርያት ምሳሌ ነው።

❖ የድምጽ ሳጥን (ገበቴ)

ከአንድ ወጥ እንጨት ተፈልፍሎ(ገበቴ) ወይም የጣውላ እንጨቶችን በማገጣጠም እና የደረቀ ቆዳ ተፍቆና ተዳምጦ በማልበስ የሚሠራ ነው። የሚለብሰው ቆዳም አገልግሎት ድምፅን ማስተላለፍ ሲሆን፤የበገናው ድምፅ የሚወጣውም ከዚህ ሳጥን ነው።(እንደ ሲንትያ ኪምበርሊን ጥናት ከዋነዛ ከሚሰሩ የበገና ክፍሎች አንዱ ነው ትላለች)

ምስጢሩ፡-

- የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ነው። ከድምጽ ሳጥኑ (ገበቴው) የበገናው ድምጽ እንደሚገኝ ከእመቤታችን አካላዊ ቃል ወልድ ጌታችን መድኃኒታችን እና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ መገኘቱን ያጠይቃል።

❖ ብርኩማ

ትንሽ ዱካ መሳይ ከእንጨት የሚሠራ ሲሆን፤ይህም ዐሥሩን እንዚራዎች ለማስቀመጥ ያገለግላል።በድምፅ ሰጥኑና በአውታሩ መካከል በመግባት እንዚራና አውታሩ በርሱ ላይ ተቀናብረው የንዝረትን ድምፅ እንዲፈጥሩ ያገለግላል። ይህም ድምፅ ደግሞ ወደ ገበቴው ገብቶ ጎልቶ እንዲሰማ ያደርጋል።

ምስጢሩ፡-

- ኑብዩ ሙሴ ዐሥርቱን ትዕዛዛት ከእግዚአብሔር የተቀበለበት የደብረሲና ተራራ ምሳሌ ነው

❖ እንዚራ

ከቁርጥራጭ ቆዳዎች የሚሠራ ሲሆን በገና በሚደረደርበት ጊዜ አውታሮቹ ድዝዝዝ.... እና ጥዝዝዝ.... የሚል የንዝረት ድምፅ እንዲያወጡ የሚያደርግ ነው።ቦታውም በርኩማ ላይ ሲሆን ፤ አውታሮቹ በርኩማ ላይ አርፈው በሚያልፉበት በሚሸፍኑት ርቀት አማካይ ላይ በአውታሩና በበርኩማው መካከል በመግባት ከፍና ዝቅ አድርጎ በማስተካከል ተፈላጊውን የንዝረት ድምፅ እንዲሰጡ ያደርጋል።

ምስጢሩ፡-

- እንዚራ ተጋድሎ ላይ ባሉ ክርስቲያኖች ይመሰላል። እንዚራ በዐሥሩ አውታር ላይ እንዳሉ፤ ክርስቲያኖችም ዐሥሩ አውታር የተመሰሉባቸውን አጠቃላይ ትዕዛዛተ እግዚአብሔርን መሪ በማድረግ፤ በዓለም ኑሯቸው መንፈሳዊ ሕይወትን ለማበልፀግ ይጋደላሉና ነው።

❖ መወጠሪያ

ከእንጨት የሚሠራ ሲሆን ከታችኛው የበገና ክፍል የሚገኝ ሆኖ አውታሮቹን ከቀንበሩ ጋርለመወጠር ይጠቅማል።

ምስጢሩ፡-

- መወጠርያ በሰዎች መኖርያ /ምድር/ ምሳሌ ነው።
- መወጠሪያ በምድር ላይ ያሉ የአዳም ዘር (የሰው ልጆች) ምሳሌ ነው። ዐሥሩ አውታሮች ቀንበሩንና፣መቃኛውን፣መወጠሪያውን ማገናኘታቸው አንዳች ትምህርት ያለው ነው። ይህም "የሰው ልጆች (መወጠሪያ) በትዕዛዛተ እግዚአብሔር (አውታር) መሰላልነት ከምድር መኖሪያቸው (መወጠሪያ) ተጋድሎዋቸውን

ጨርሰው (መቃኛ) ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመግባታቸው እና ከፈጣሪያቸው እግዚአብሔር (ቀንበር) ጋር ለዘለዓለም በደስታ የመኖራቸው ምሳሌ ነው።

❖ የመወጠሪያ ጠፍር

ዐሥሩን አውታሮችን የያዘ ከእንጨት የተሠራውን አግዳሚ መወጠሪያ ከግራ እና ከቀኝ በመሆን ከበገናው የድምጽ ሳጥን ላይ ወጥሮ የያዘ ከቆዳ የሚሠራ ጠፍር ነው። የብዙዎቹ የጥንት በገኖች መወጠሪያ ጠፍር የድምጽ ሳጥኑን(ገበቴውን) ከላይ ያለበሰውን ቆዳ በመብሳት ከውስጠኛው የድምጽ ሳጥን ክፍል ላይ የሚታሰሩ(የሚመቱ) ሲሆን በአሁን ጊዜ ያሉት በገናዎች ደግሞ ይህንኑ ጠፍር ከድምጽ ሳጥኑ የውጪኛው ክፍል ላይ በሚስማር የሚመታ ተደርገው ይበጃሉ።

ምስጢሩ፡-

- የእግዚአብሔርን ዙፋን የተሸከሙት የኪሩቤል (ኪሩብ) ምሳሌ ነው

❖ ድሕንጻ(መግረፊያ)

ከቀንድ ወይንም ከእንጨት የሚሰራ መግረፊያ ሆኖ በግራ ምሰሶ ላይ የሚታሰር ሲሆን አገልግሎቱም ዐሥሩን አውታሮች ከወዲያ ወዲህ እያለ በመግረፍ ልዩ ድምፅ እንዲሠጡ የሚያደርግ ነው

ምስጢሩ፡-

- ድሕንጻ በክርስቶስ ይመሰላል። ድኅንጻ ዐሥሩን አውታሮች እየተመላለሰ እንደሚገርፋቸው፤ መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስም በብሉይ ኪዳን የሰጣቸውን ዐሥሩን ትዕዛዛት በሐዲስ ኪዳንም አጽንቷቸዋልና።

❖ ማረኛ

የድምጽ ሳጥኑን (ገበቴውን) ያለበሰውን ቆዳ ዙሪያውን ወጥረው በመያዝ ከገበቴው ላይ ረግቶ እንዲቀመጥ እና እንዳይረግብ ያደረገው ጥልፍልፍ ስፌት ነው።

ምስጢሩ፡-

- ምድርን ተሸክመው ባሉ ብሔሞት እና ሌዋታን የሚባሉ ግሩማን ዘንዶዎች ምሳሌ ነው።።

❖ ከድምጽ ሳጥኑ (ገበቴው) ጀርባ ላይ ያለው የመስቀል ቅርጽ

ከበገናው ጀርባ የሳኦል ጦር የበሳው ቀዳዳ ቅዱስ ዳዊትን መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል ነግሮት ከተወረወረበት ጦር በበገናው አማካኝነት መክቶ የዳነበት ምልክት ሲሆን መስቀል በሐዲስ ኪዳንም ከድያብሎስ ፍላፃ የዳንበት (የምንድንበት) ምልክታችን በመሆኑ ይህ ምልክት ተደረጓል።።

የበገና አሰራር

በገና ከእንስሳትና ከእጽዋት ተዋጽኦ የሚሠራ የዜማ ዕቃ ነው።። ቁመቱ ከ90 ሳ.ሜ. እስከ 140 ሳ.ሜ. ይደርሳል።። ነገር ግን እንደ ሠሪውና እንደ አሠሪው ፍላጎት ሊጨምር /ሊቀንስ/ ይችላል።።

ለምሳሌ፡- ከእንስሳት ተዋጽኦ፡-

አውታር (ጅማት) = ከበግ አንጀት/ ከበሬ፣ ከላም ጅማት

ቆዳ = የድምጽ ሳጥኑ የሚለብሰው እና መወጠሪያውን የሚያስረው ፦ ከበሬ፣ ከላም፣ ከበግ፣ ከፍየል ቆዳ

እንዚራ = ከበሬ (ከላም) ቆዳ

ድህንፃ= ከበሬ (ከላም) ቀንድ

ከእጽዋት ተዋጽኦ፡-

ከእጽዋት ተዋጽኦ ማለትም ከዋንዛ፣ ከቀረሮ፣ ከዝግባ፣ ከጽድ ወ.ዘ.ተ. የሚሠሩ የበገና ክፍሎች ቀንበሩ(ጋድም)፣ ምሰሶዎቹ፣ የድምጽ ሳጥኑ፣ ብርኩማው፣ መቃኛው፣ ጌጡ እና መወጠሪያው ናቸው። ይህ የዜማ ዕቃ ቁሶቹን ከማለዘብ፣ ከማለስለስ፣ ጌጥ ከመቅረጽ፣ ለአያያዝ እንዲመች ከማድረግና ውበት ከመስጠት ውጪ ከተፈጥሮ ከተገኙ ቁሶች የሚሠራ ነው። በመሆኑም የሚያወጣው ድምጽ፣ የሚሰጠውም ዜማ ተፈጥሮአዊ ነውና መንፈስን ይማርካል፣ ነፍስን ያስደስታል።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ወለወላዲቱ ድንግል

ወለመስቀሉ ክቡር አሜን!!!

ዋቢ

- ሚሊዮን በለጠ አሰፋ ፤ ንዋየ ቅድሳት ፤ 3ኛ ዕትም ፤ 2006 ዓ.ም።
- የበገና መማሪያ መጽሐፍ ማኅበረ ቅዱሳን